# “ትራውማ” በመረቅ ውስጥ[1]

እየሩሳሌም ዳኜ*

**አጠቃሎ**: ይህ ጥናት በ2007 ዓ.ም. በታተመው የአዳም ረታ ልብ ወለድ፣ መረቅ ላይ በዘመናዊው “የትራውማ ንድፈ ሐሳብ” የታገዘ ንባብ በማድረግ የትውልድን የልቡና መታወክ (ትራውማ) ለመፈተሽ የሞከረ ነው፡፡ የትራውማ መፈጠሪያ ምክንያቶችና መከሰቻዎች፣ የተስተማስሉባቸውን ትዕምርቶችና ገጸ ጽሑፋዊ አቀራረቦች በመመርመር ዘመኑን የመፈከር፣ ትውልድ ዘለል ቀውሶቹን የማሳየት ዓላማ አለው፡፡ በውጤቱ ሕማሙ ያስከተለው ጉዳት በግለሰብ ሳይወሰን ወደ ማህበረሰብ መዝለቁ ታይቷል፡፡ የጉዳቱን ሰንሰለት ያራዘሙና የትራውማን ከትውልድ ወደ ትውልድ ተሸጋጋሪነት ያሳዩ መንገዶች መኖራቸውንም ማጤን ተችሏል፡፡ መረቅ በመረጠው የትረካ ስልት እና በተገለገለባቸው ልዩ ልዩ ገጸ ጽሑፋዊ አቀራረቦች እንዲሁም ትዕምርቶች ትራውማን በወጉ ነድፎ ማሳየት የቻለ ነው፡፡ በእነዚህ ስልቶች አማካይነት ለገጸ ባሕርይዎቹ የሥነ ልቡና ጉዳትና ትግል ምስል በመፍጠር ረቂቁንና ውስብስቡን ሥነ ልቡናዊ ቁስል ተጨባጭ አድርጓል፡፡ በጥቅሉ መረቅ ዘመንና ትውልድ እየተሻገረ በመጣ ጥርቅም ትራውማ ልቡናቸው ታውኮ፣ ዛሬያቸውን በራሳቸው መልክና ጣዕም መኖር ያልቻሉ፣ በትላንትና ዛሬ መኃል ባክነው የቀሩ ገጸ ባሕርያት ሥጋና ነፍስ የነሱበት የዚያ ዘመን አንደበት መሆኑን ማሳየት ችሏል፡፡ የገጸ ባሕርያቱ ከዛሬ ይልቅ በትላንታቸው ተጠምደው መታየት የትውስታ አንድ (ሌላ) ጎን የሆነውን ኖስታለዥያ (nostalgia) ርዕሰ ጉዳይ አድርጎ ለማጥናት ጋባዥ ሆኖም ይታያል፡፡

## መግቢያ

አዳም ረታ፣ የአንድን ትውልድ የወል ልቡና፣ የጋራ ትውስታና ሰብአዊ ዕጣ ከፍ ባለ ኪነት ከነደፈባቸው ልብ ወለዶች መካከል አንዱ መረቅ ነው፡፡ መረቅ (2007 ዓ.ም.) በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ በአወዛጋቢነቱና በአከራካሪነቱ የሚታወቀው፣ ከ1950ዎቹ ማብቂያ እስከ 1970ዎቹ የገነነው ወጣት ትውልድ ስንክሳር ሥነ ልቡናዊ ፍካሬም (psychologizing of history) ነው ማለት ይቻላል፡፡[2] ይህ የእኔ መጣጥፍ በዘመናዊው “የትራውማ ንድፈ ሐሳብ” በመታገዝ በልብ ወለዱ ውስጥ የተቀረጸውን የትውልዱን የልቡና መታወክ (ትራውማ) ለመመርመር የሚሞክር ነው፡፡

መረቅ ከ1966ቱ የአገራችን የመንግስት ለውጥና አብዮት ጋር ተያይዞ የተከሰቱትን ድንገተኛና ያልተለመዱ ሁኔታዎች በሚገባ አስተማስሎ የሚያሳይ ኪነት ነው ማለት ይቻላል፡፡ እንደ አብዮት፣ መፈንቅለ መንግስት እና ጅምላ ግድያ የመሳሰሉ ክስተቶች ካላቸው ትራውማን የመፍጠር ሰፊ እድል አንጻር በቀዳሚነት ይቀመጣሉ (Sztompkan 2000፡ 451)፡፡ በዚህ መልኩ ሲታይ ከአብዮት ተያያዥ በሆኑ ግለሰባዊና ማኅበራዊ ሁነቶች የተሞላው መረቅ ለትራውማና መሰል ጥናቶች እጅጉን ምቹና ጋባዥ ይሆናል፡፡ ይህም ጥናት በዘመናዊ ትራውማ ንድፈ ሐሳብ ማቀንቀኛትነት የትራውማ መፈጠሪያ ምክንያቶችን፣

---

[1] ይህ መጣጥፍ፣ በ2008 ዓ.ም. “ ‘ትራውማ’ በመረቅ ውስጥ፤ በይነ ዲሲፕሊናዊ ጥናት” በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት ካቀረብኩት ጽሑፍ ተወስዶ፣ ለዐውዱ እንዲስማማ ሆኖ የቀረበ ነው፡፡

* በአዲስ አበባ ዩኒበርሲቲ በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪና በክሩዝ ትምህርት ቤት የሚዲያና ተግባቦት ባለሙያ፡፡

[2] ቴዎድሮስ ገብሬ የአማርኛ ሥነ ጽሑፍን በሥነ አእምሮ አንጻር የመመርመር ተገቢነትን ባመለከተበት ጥናቱ “ከ2000 ዓ.ም. በኋላ በ ‘ያ ትውልድ’ አባላት ተጽፈው እየታተሙ ከሚወጡ ባዮግራፊ ነክ ድርሰቶች እኩል የአዳም ኋለኛ ልብ ወለዶች (በተለይም እቴሜቴ ሎሚ ሽታ፣ ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ እና መረቅ) የትውልዱ የልቡና ቀውስ (“ኖስታልዥያ፣ ፖስት ትራውማቲክ ስትረስ ዲስኦርደር፣ ቪክትም ሜንታሊቲ--እጅጉንም ሰልፍ ኤማጂኒንግ ቪክቲማይዜሽን”) በምልዓት የተነደፈባቸው ኪነቶች መሆናቸውን ያስረዳል (2007፡ 9)፡፡

የተስተማሰለባቸውን ትዕምርቶችና ገጸ ጽሑፋዊ አቀራረቦችን በመመርመር ዘመኑን የመፈከር፣ ትውልድ ዘለል ቀውሶቹን የማሳየት ዓላማ አለው፡፡

## ትራውማና የትራውማ ንድፈ ሐሳብ

ትራውማ ከተለመደው የአኗኗር ልማድና እምነት ውጭ የሆነ ያልተጠበቀና አስደንጋጭ ሁኔታ ሲገጥም ለሁኔታው ያልተዘጋጀ ልቡና ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡ ለጉዳቱ መነሻ የሚሆነው ክስተት ሰው ሰራሽ (atrocities) ወይም ተፈጥሮ አመጣሽ (disasters)[3] ሊሆን ይችላል፡፡ ሁነቶቹን በተለየ ለትራውማ መቀስቀስ ምክንያት የሚያደርጋቸው ዋነኛ ነገር ለረዳት አልባነትና ለሽብር የመዳረግ ኃይላቸው ነው፡፡ እንዲህ ያሉ ሁኔታዎች ሲገጥሙ የተለመደው ምላሽ ነገሩን ከንቁ አእምሮ ማሸሽ ቢሆንም በትራውማ ግን ይህ የሚቻል አይደለም፡፡ አዳፍኖ አልያም አሸሽቶ ማስቀረቱ አይሳካም፤ አሸንፎ ይወጣል (Herman 2015)፡፡

ሁኔታው ባጋጠመ ወቅት በሚፈጠረው ከፍተኛ ድንጋጤ የተነሳ አእምሮ ነገሩን በቅጡ ለማብላላትና ለመረዳት ይሳነዋል፡፡ ምናልባትም ምን እንደተፈጠረ ሳይገነዘብ ሊቀር ይችላል፡፡ ይህም ሆኖ ትውስታው በኢ-ንቁ አእምሮ ውስጥ መሸጎ ይቀመጣል፡፡ ቆይቶ ከንቁ አእምሮ የሸሸው የገጠመኙ ትውስታ አንዳች አንቂ ወይም ቀስቃሽ ሲያገኝ ከግለሰቡ ቁጥጥርና እውቅና ውጭ እየተመላለስ ይመጣል፡፡ በዚህ የተነሳ ተጎጂው ሁነቱ ሲገጥመው በነበረው አስጨናቂ ስሜት ውስጥ መልሶ መላልሶ በመግባት እየተረበሸ እንዲኖር ይገደዳል፡፡ በCaruth አገላለጽ ተጎጂው “ባለፈ ሁነት ወይም ምስል ቁጥጥር ስር ይውላል”(1995፡ 4-5)፡፡

የትራውማ ትውስታ ከጤነኛው ትውስታ ይለያል፡፡ ምክንያት የነበረው ሁነት እንደ ተለመዱ ሁነቶች በቀላሉ የሚገነዘቡትና ትርጉም አበጅተው የሚያልፉት አይደለም፡፡[4] ትውስታውም ከተለመደው ሥፍራና ሁኔታ በተለየ ከንቁ አእምሮ ቁጥጥርና ግንዛቤ ውጭ የሚቀመጥ ነው፡፡ በመሆኑም ሊገነዘቡት የማይቻል፣ ለትረካ የማይታዘዝ ወይም ለቋንቋ የማይገዛ ይሆናል (Moran 2007: 5)፡፡ ጤነኛ ባልሆነ መልክ የተመዘገበው የሁነቱ ትውስታ በንቃት እንዲሁም በእንቅልፍ ጊዜ ድንገት ወደ ንቁ አእምሮ ዘው እያለ ወደ ሁነቱ ይመልሳል (Herman 2015: 37)፡፡ በዚህ መንገድ የትውስታው ያለ ፍላጎት ተደጋግሞ መምጣት የትራውማ ዋና መገለጫ ነው፡፡

በዚህ መልኩ የሕመሙ ምልክት መታየት እስኪጀምር ግን ጊዜ ይወስዳል፡፡ ወይም በገጠመኙና በምልክቶቹ መገለጥ መኃል የጊዜ ርቀት ይኖራል፡፡ ይህ በገጠመኙና በምልክቶቹ መታየት መጀመር መኃል ያለ የጊዜ ርቀት ወይም ክፍተት (belatedness)[5] ሌላው የትራውማ ሕማም መለያ ባሕርይ ነው፡፡ በሚከተለው የCaruth ሐሳብ ውስጥ እነዚህን ዋነኛ የትራውማ ባሕርያት ማጤን ይቻላል፤ “[T]rauma describes an overwhelming experience of sudden or catastrophic events in which the response to the event occurs in the often delayed, uncontrolled repetitive appearance of hallucinations and other intrusive phenomena” (1996: 11)፡፡

---

[3] Herman እንደ መሬት መንቀጥቀጥ፣ አውሎ ነፋስና ጎርፍ ያሉ ለትራውማ አጋላጭ የተፈጥሮ ሁነቶችን ‘disasters’፤ እንዲሁም እንደ ጦርነት፣ የሽብር ጥቃት እና ጾታዊ ጥቃት ያሉ ለትራውማ አጋላጭ ሰው አመጣሽ አደጋዎችን ደግሞ ‘atrocities’ በማለት ይለያሉ (2015፡ 33)፡፡

[4] ተራና ተለምዷዊ ከሆኑ ሁነቶች ወዲያው ትርጉም ማበጀት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በቀላሉ ለመገምገምና ለመገንዘብ ስለሚቻል፡፡ የዚህ አይነት ሁነቶች ግምገማና ግንዛቤው ቆም ብሎ ማሰብን እንኳን ሳይጠይቅና ልብ ሳይባል የሚከናወን ነው፡፡ ትራውማዊ ሁነቶች ግን ከዚህ ይለያሉ፡፡ እንዴት? ለምን? ብሎ በመጠየቅ ምላሽ ለማግኘትና ትርጉም ሰጥቶ ለማለፍ የሚቀሉ አይደሉም፡፡ ይህ ደግሞ በቀጥታ ከትራውማዊ ሁነት ትውስታ ለቋንቋ አለመገዛትና ለትረካ አለመታዘዝ ባህርይ ጋር ይያያዛል፡፡

[5] Belatedness የገጠመኙ ተጽእኖ ግልፅ ሳይሆን የሚቆይበት ጊዜ ነው፤ ሁነቱ ወደ እመቃ (repression) ተገፍቶ ከዛም ወደ መገለጡ እስኪደርስ ያለውን ጊዜ ያሳያል፡፡ አንድ ሰው የትራውማ ታማሚ መሆኑን ለማወቅ ከገጠመው ሁነት በኋላ ይህን የጊዜ ቆይታ ማለፍና ምልክቶቹን ማየት ይጠይቃል፡፡ ምክንያቱም የአንድ ሰው ሥነ ልቡናዊ አወቃቀሩና የሕይወት ልምዱ ከሌላው የተለየ በመሆኑ አንዱን ለትራውማ የዳረገ ገጠመኝ ሌላውን ላይዳርገው ወይም ሊቋቋመው ይችላል፡፡

በትራውማ ታማሚ የሆነ ሰው አደጋው በየትኛውም ቅጽበት ተመልሶ ሊከሰት ይችላል በሚል ስጋትና ራስን የመጠበቅ ንቃት (hyper arousal) ውስጥ ይገባል፡፡ ከረጅም ጊዜ በኋላም ያለማቋረጥ በሚመጣ የሁነቱ ትውስታ የተነሳ ትራውማዊ ቅጽበቱ ውስጥ መልሶ መላልሶ እንዲገባ ወይም እንዲኖር (intrusion) ይሆናል፡፡ በተጨማሪ ከገባበት አጣብቂኝ መውጫ ከማጣት የተነሳ አቅምና ረዳት አልባነቱን ስለሚቀበል የአእምሮው ንቃት በምርኮኛነት ስሜት እጅ ወደ መስጠት (constriction) ይለወጣል፤ወይም የሚሆነውን ነገር ስሜት አልባ ሆኖ ማስተናገድ ውስጥ ይገባል (Herman 2015: 36)፡፡ በዚህ ዓይነት ተጎጂው ለእንቅልፍ መረበሽ እና ሲከፋም ለእንቅልፍ ማጣት ይዳረጋል፡፡ በህልሙና ቅዠቱ፣ ምኞትና ተስፋው ሁሉ ከክፉ ገጠመኙ እየሄደ ይላተማል፡፡ ዛሬ ላይ እየኖረ መለኪያ ሚዛኑ፣ መመልከቻ መነፅሩ ትላንትና ክፉው ሁነት ይሆንና የዛሬ ምንነትና ጣዕም ይጠፋዋል፡፡ በትላንትና ዛሬው መኃል መለያው ጠፍቶት ከራሱ ጋር ስምምነት ያጣል ወይም ማንነቱ ይቃወሳል፡፡ እጅግ ስጉነትና ጠንቃቃነት አልያም እጅግ ግዴለሽነትና ስሜት አልባነት ይነግስበታል፡፡ ለአለምና ለራስ ያለው ግምትና አስተሳሰብ ይቀየራል- ክብርና ትርጉም አልባ ይሆንበታል፡፡ በጥቅሉ ሕይወቱ ይቃወሳል፡፡

እንዲህ ያሉትን ሕመሙ የሚያስከትላቸው ምስቅልቅሎች ምንነትና ምክንያት ለመረዳት እንደ ሌሎቹ የልቡና መታወኮች ሁሉ የተጎጂዎቹን ስሜትና ባሕርይ እንዲሁም ያለፈ ታሪክ ማጤን ይጠይቃል፡፡ ታማሚዎቹ ራሳቸው እየሆኑ ያሉትን ካለፈ ገጠመኛቸው አገናኝተው በማሰብ ችግራቸውን የሚረዱትና የሚገልጹት አይደለም፡፡

ግለሰብ፣ ማኅበረሰብ፣ ባህል፣ የፖለቲካ ሥርዓት ወዘተ ለትራውማ መፈጠር ምክንያት ሊሆኑ የመቻላቸውን ያህል ተጠቂዎችም ይሆናሉ፡፡ አንድ ግለሰብ በትራውማ ሲጠቃ የስሜት፣ የእውቀት፣ የትውስታ፣ የአኗኗር፣ የአመለካከት፣ ወዘተ ለውጥ ያመጣል፡፡ ጉዳቱ ከግለሰብ ባለፈ የወል (collective/mass trauma) ሆኖ በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ሲፈጠር ደግሞ መረብ ሆኖ ማኅበረሰቡን በአንድ የሚያያይዘውን የጋራ እምነት፣ አስተሳሰብ፣ ባህል፣ ታሪክ ወዘተ ስለሚጎዳ የጋራ (የአንድነት) ስሜት ይጠፋል፡፡ እንዲህ ያለው ትራውማ የተጠራቀመ የሥነ ልቡና ጉዳት ሲሆን ጊዜና ትውልድ ተሻግሮ ለሌላ ትውልድ የመድረስ አቅም ያዳብራል፡፡ የቀደመው ሳይፈታ ሌላ እየተደራረበና እየተጠራቀመ የሚመጣ በመሆኑ ደግሞ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ እና በቀላሉ የማይወገድ ውጤት ያስከትላል፡፡ ትራውማ በእርስ በርስ ግንኙነቶች የተመሰረተ አኗኗር ላይ የሚያስከትለውን ጥፋት ቀዳሚና ዋነኛ አድርገው የሚከራከሩት Herman መሰረታዊ የሰው ልጅ ግንኙነትን ጥያቄ ውስጥ የመጣሉን ሁኔታ አጽንኦት ይሰጡታል፡፡ በትራውማ ከቤተሰብ፣ ጓደኛ፣ ፍቅረኛ እና ማህበረሰብ ጋር ያለ ቁርኝት እንደሚበጠስ፤ ከሌሎች ጋር በሚኖር ግንኙነት የሚደረጀው የእኔነት (self) ግንባታ እንደሚሰናከል፤ የሰው ልጅ ለገጠመኞቹ ትርጉም የሚያበጅበት የእምነት ሥርዓት እንደሚፈርስ፤ የተጎጂው እምነትና የመኖር ህልውና እንደሚቃወስ ያስረዳሉ (ዝኒ ከማሁ 51)፡፡ በጥቅሉ እንደ Bell አገላለጽ የትራውማ ጉዳት የልቡና፣ የማኅበረሰብ፣ የባህልና የአካባቢ ጉዳት ጭምር ነው ("[Trauma is] an injury to the psyche, or even the community, the culture, or the environment") (2006: 7)፡፡

ሕማሙ በቤተ ሙከራ ምርመራ የሚገኝ (diagnostic) ሳይሆን በባሕርያቱ ምሪት የሚደረስበት (symptomatic) ነው (Luckhurst 2006: 504)፡፡ በዚህ ላይ የመነሻ፣ የመድረሻና የመገለጫው ውስን አለመሆን ታክሎበት በእእምሮ ሕክምና እውቀት ብቻ የሚመረመር እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ የትራውማ ገጠመኝ የሚያስከትለው ነውጥና የሚፈጥራቸው ክፍተቶች ፍካሬ ልቡናን (psychoanalysis)፣ የእእምሮ ሕክምናን (psychiatry)፣ የማኅበረሰብ ጥናትን (sociology) እና ሥነ ጽሑፍን እርስ በርስ ወደ መደማመጥ አምጥቷቸዋል፡፡ ይህ በዲሲፕሊኖች መኃል የመጣ መናበብ በትራውማ ጥናት ላይ አዲስ እመርታ ማስገኘቱንና በዚህ የተነሳም ትራውማ ሁሉን አካታች "all-inclusive" ወደ መሆን መሸጋገሩን Caruth ያስረዳሉ (1995: 4)፡፡ በLuckhurst አባባል ደግሞ ትራውማ በተፈጥሮው በይነ ዲሲፕሊናዊ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ጥናቱም በርካታ የእውቀት ዘርፎችን በማካተት በትራውማ ተፈጥሮና የትራውማዊ ሁነቶች አስተማስሎ ላይ የሚያተኩር ሊሆን በቅቷል "Trauma study now includes many fields,

focusing on psychological, philosophical, ethical, and aesthetic questions about the nature and representation of traumatic events" (2006: 497)።

ጅምሩ ላይ የነበረው አውሮፓዊ፣ ግለሰብ ተኮርና ሥነ ልቡናዊ የትራውማ አረዳድና አተረጓጎም አፍሪካን ጨምሮ ለሌሎች ባህሎችና እውቀቶች ሥፍራ አልነበረውም። በአውሮፓዊ ባህልና ሥነ ልቡና ላይ ብቻ የተወሰነውን የሕመሙ መፈጠሪያ ምክንያትና ጉዳት ሁለንተናዊ በማድረግ ሌሎችን በዚያ ለመስፈር የሚጥር ነበር። በኋላ ላይ ግን ሁነቱ የሚፈጠርበትን ባህልና ማኅበረሰብ ያገናዘበ፣ ከግለሰብ ባሻገር የወል ግንኙነትና ጉዳትን ከግምት ያስገባ አረዳድ ሊዳብር ችሏል። በዚህ ምክንያት የትራውማ ንድፈ ሐሳብ ለተረሱና ለተገፉ ማኅበረሰቦች የሕይወት ልምድና ሕማም የመነገርና የመደመጥ እድል ጭምር ፈጥሯል ማለት ይቻላል።

ሥነ ጽሑፋዊው የትራውማ ንድፈ ሐሳብ በበኩሉ ትራውማን ከሥነ ልቡና አንጻር ብቻ ከመመልከትና ከመፈከር ወጥቶ ወደ በይነ ዲሲፕሊናዊነት ተሻግሯል። ሒሱም ሥነ ምግባራዊ፣ ተጠያቂነት ያለበት፣ ጠቃሚ (ethical, responsible, purposive) እንዲሁም የሌሎችን ቁስል ማዳመጫ ሐቲት ለመሆን በቅቷል (ዝኒ ከማሁ 505)። ኋላ ላይ የተዋወቁትን የትራውማን ተግባር በሥነ ጽሑፍና በማኅበረሰብ ውስጥ መመልከት የሚያስችሉ ንድፈ ሐሳባዊ ስልቶችና ሒሳዊ መንገዶች ከቀደሙት አጥኚዎች እሳቤ የተለዩና የተሻሉ መሆናቸውን Balaeveም ይመሰክራሉ (2014: 3)።

ሥነ ጽሑፋዊው የትራውማ ንድፈ ሐሳብ በማኅበራዊ እና ባህላዊ አውድ ላይ አትኩሮ ትራውማን በሥነ ጽሑፍ ውስጥ መፈተሽን ያለማመደ ነው። Summerfield እንደሚያሳስቡት ከትራውማ ገጠመኝ የተያያዙ ፍቺዎችን ፍለጋችን ግለሰብ ከማኅበረሰቡ ጋር ያለውን ግንኙነት በባህል፣ በማኅበረሰብ እና ፖለቲካዊ ኃይሎች ተጽእኖ ከሚመጡ ውጤቶች ጋር ያገናዘበ ሊሆን ይገባል (1995፡ 27-8)። ምክንያቱም የሁነቱ አይነትና የተጽእኖው መገለጫ መልክ ተጎጂው እንደሚኖርበት ባህል፣ እምነትና የአኗኗር ሁኔታ ስለሚለያይ ነው። ይህ ሲባል ግን አንድ ባህል ወይም ማኅበረሰብ በራሱ ዙሪያ ብቻ ታጥሮ ጉዳዩን ይመረምራል ወይም ይረዳል ማለት አይደለም። ራስንም ሌላውንም በአንድ ጊዜ መመልከትና መመርመርን ይሻል ማለት እንጂ።

ንድፈ ሐሳቡ የትራውማን ለቋንቋ ያለመገራትና ለትረካ ያለመታዘዝ ባሕርይ ከሥነ ጽሑፍ የአስተማስሎ ኪን ጋር አስማምቶ መያዝ የቻለ ነው። ትራውማ በአንድ በኩል ለቋንቋና ትረካ የማይታዘዝ ነው። በሌላ በኩል ድብቅና አይደረሴ የሆነ ሥነ ልቡናዊ ጉዳቱ ድምጽና ምስል አግኝቶ በሥነ ጽሑፍ ይገለጻል። ሥነ ጽሑፍ ይህን ተቃርኖ አስታርቆ ትራውማን መርታት የቻለበት ልዩ መንገዱ አስተማስሎ ነው። በግልጽና በቀጥታ አልነገር ባዩ ትራውማ ለሥነ ጽሑፍ የአስተማስሎ ኃይል እጅ ይሰጣል። በዚህ መንገድ በተለያዩ ነገሮች ተስተማስሎ በፍካሬ ይደረስበታል እንጂ በግልጽና በቀጥታ የሚገለጽ አይደለም።

ይህ ጥናት በልብ ወለዱ ላይ የሚያደርገውን ትንተና ከሥነ ጽሑፍ፣ ከሥነ ልቡና፣ ከባህል፣ ከማኅበረሰብና ከታሪክ በተቀዱ ሐሳቦች አስተጋግዞ ለማካሄድ የሚሞክር በመሆኑ በይነ ዲሲፕሊናዊ መልክ ይኖረዋል። ልብ ወለዱ የተተረከበትን መንገድ፣ የተገለገለባቸውን ገጸ ጽሑፋዊ አቀራረቦች ወዘተ ከትራውማ መገለጫ ባሕርያትና ከሚያስከትለው ቀውስ ጋር በማስተሳሰር፣ በመተንተንና ትርጉም በማበጀት ይዘልቃል።

## የትራውማ መንስኤዎች እና ጅምር መታያዎች

የመረቅ ታሪክ ከ1950ዎቹ እስከ 1970ዎቹ አጋማሽ ባሉት ጊዜያት ውስጥ የተዘረጋ ነው። በተለይ የ1966ቱን የመንግስት ለውጥና የተከተለውን ግጭትና ውጥንቅጥ ዋናው ማዕከሉ አድርጓል። የልብ ወለዱን ገጸ ባሕርያት ከትራውማ አንጻር የማጤን ዋነኛው ምክንያትም ይኸው የኖሩበት ዘመን ማኅበረ ፖለቲካዊ ቀውስ ነው። "All trauma is to some extent determined by political forces, effects, and motives" (1995: 7) ከሚለው የእነ Kleber ሐሳብ በተስማማ መልኩ በልብ ወለዱ የሚስተዋለው

ትራውማ የዘመኑ ፖለቲካ አስተዋጽኦ የጎላበት ነው፡፡ ግለሰባዊ መስለው የሚታዩት የትራውማ መንስኤዎች ሳይቀር በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ከዘመኑ ፖለቲካዊና ታሪካዊ ሁነት ጋር ይያያዛሉ፡፡

የገጸ ባሕርያቱ በትራውማ ተጠቂ መሆን በድርጊትና በንግግር በሚመሳከሩ የባሕርይና የስሜት ለውጦቻቸው አማካይነት ይታያል፡፡ በልብወለዱ ውስጥ፣ ለፖለቲካው ፍላጎትም ተሳትፎም የሌለው አልዓዛር ተደጋጋሚ ለሆኑ የትራውማ መንስኤዎች የተጋለጠ ነው፡፡ ጓደኛው ደበበ የሞተበት ሥፍራ ላይ ደርሶ የሚያየው አስደንጋጭ ትዕይንት፣ ሚች ጓደኛው ቤት ሄዶ የሚገጥመው የቤተሰቦቹ ሀዘን፣ ለወዳጁ ሞት የቅርብ የሚባል ሰው ምክንያት መሆኑን መስማቱ ወዘተ ተደራርቦ ስሜቱን ያመሳቅለዋል፡፡ በድንጋጤ፣ በሀዘን፣ በፍርሃት፣ በጥርጣሬ፣ በጥያቄ ጭምር ይዋጣል፡፡ የደረሰበትንና የገባበትን ሁኔታ ራሱ "ሁሉ ነገር ሲሰበሰብ የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ እንደመዋጥ ነው" (109) ሲል ይገልጸዋል፡፡

አላዛር ለእነዚህን መሰል ድንገተኛ ነገሮች በተደጋጋሚ ይጋለጣል፡፡ በሌላ ምሽት በአካባቢው ተሰምቶ የማያውቅ ዐይነት ኡኡታ ሰምቶ፣ እንዳይወጣ የምትከለክለውን ተባረኪ አሽንፎ ይወጣል፡፡ ከጩኸቱ ስፍራ ሲደርስ የሚገጥመው እጅግ ያልጠበቀው ነገር ይሆንና ድንጋጤው ልክ ያጣል፡፡

> [. . . ] *መንገድ ዳር እግሮቹ ወደ አስፋልቱ ጭንቅላቱ ደግሞ ወደ ቦይ ሆኖ የወደቀ ሰው አየሁ፡፡ ከአስፋልቱ በኩል ስለመጣሁ በደብዛዛው የመንገድ ብርሃን የወደቀው ሰው ምን እንደሆነ መለየት አልቻልኩም፡፡ ቆሞ የሚጮኸውን ሰውዬና የምታለቅሰውን ሴትዮ ግን አውቃቸዋለሁ፡፡ እነሱን ሳይ የልቤ ምት ለአፍታ ሲቆም ተሰማኝ፡፡ እነዚህን ሰዎች ሲጮኹ ከዚህ በፊት አይቼአቸው አላውቅም፡፡ ሌላ ፕላኔት፣ ሌላ አህጉር የገባሁ መሰለኝ፡፡ ሕልም መሰለኝ፡፡ ለአፍታ ቀጥ ያለው ልቤ በፍጥነት መንተክተክ ጀመረና አቅለሸለሸኝ፡፡ አዞረኝ፡፡ በቀስታ እየተራመድኩ በሆዴ 'ጂሰስ ጂሰስ ጂሰስ' እያልኩ ወደ ወደቀው ሰውዬ ተጠጋሁ፡፡ ከአናታቸው ስር ደም ይወርዳል፣ አፋቸውን ወደ ሰማይ ከፍተዋል* [. . . ] (118፡ *አጽንኦቱ የእኔ ነው*)፡፡

ለዚህ አይነት ድንጋጤ የዳረገው ጎረቤቱ፣ ለእነሱ ቤት ቤተኛ እና የጓደኛው አባት ከሆኑት ሰው ሞት ጋር መፋጠጡ ነው፡፡ እኚህ ሰው ለእሱ እንዳባቱ ስለነበሩ ለሳምንት ትምህርት ቤት ሳይሄድ ሀዘን ተቀምጧል፡፡ ፀጉሩን ተላጭቶ ጥቁር ለብሷል፡፡ የተፈጠረበትን ስሜት ሲገልጽም፤ "እንኳን መማር ስለ መማር ማሰብ አስጠላኝ፡፡ [. . . ] ድሮ ባርኔጣና መላጨት አልወድም ግን እንዲህ ሲደርስና በሕይወቴ መለልታ የመክብብ መሞት አንጓ ሆኖ ሲሰነቀር፣ ሞት ፋሽን አስለወጠኝ" (119) ይላል፡፡

ከጓደኛና የቅርብ ሰዎቹ ድንገተኛና አሰቃቂ አሟሟት ሌላ በገዛ ራሱ ላይም እስርና ግርፊያ ይደርስበታል፡፡ ድንገት ከቤቱ በወታደር ተይዞ፣ አይኑ በጨርቅ ተሸፍኖ ይወሰዳል፡፡ ምክንያቱን እንኳን ሳያውቅ በሽንትና በላብ ጠረን የተሞላ ወና ክፍል ውስጥ ይታሰራል፡፡ እንደ አባቱ በሚያያቸው አቶ መክብብ ሞት እጁ እንዳለበት ተጠርጥሮ ይመረመራል እንዲሁም ይደበደባል፡፡

ከገጠሙት ድንገተኛና አሰቃቂ ክስተቶች የሚመነጨው የአላዛር የልቡና ሁከት የሚጀመረው በዚህ መልክ ነው፤

> [. . . ] *የፌሽታ ቅመም የጎደላቸው፣ ቢነገርላቸው የማያምሩ ደባሪ ጊዜያት ካልታወቀ የባዕድ ስፍራ ወደ ሕይወቴ ቀዬ መንቆርቆር ጀመሩ፡፡ መጀመሪያ እንዲህ አልፎ ሂያጅ ጎርፍ መስለው መጡ፤ ብዙ ሳይቆይ ትተውኝ የማይሄዱ ነጋ ጠባ የሚፈሱ፣ ወገባቸውን በብረት ድግ የታጠቁ ቅመማቸው የሰነሰነ፣ በርበሬያቸው የተሰለበ ጭጋጋማ አልጫ ቀናትና ሳምንታት ሆኑ* (137)፡፡

ደስታ አልባና የማያልፉ ጊዜያት ውስጥ መግባቱን ሲተርክልን ከአሰቃቂ ሁነቶቹ በኋላ የተፈጠሩበት የስሜት ለውጦች መኖራቸውን እንገነዘባለን፡፡ እንደማንኛውም የሐዘንና የድንጋጤ ስሜቶች ቀን ሲገፋ የሚቀሩ ከመሆን ይልቅ በየጊዜው የሚጠነክሩና የሚደጋገሙ መሆናቸውንም እናስተውላለን፡፡

> *ከተጋደምኩበት ወይም ከተቀመጥኩበት ስነሳ ሁለመናዬ ይደክማል፡፡ የሚያነጋግረኝ ሰው እፈልግና ስወጣ ባገኝም ዝም እላለሁ፡፡ ትምህርት ቤት ከተመለስኩ፣ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ወይም ካለቀ በኋላ ከክፍሌ ልጆች ጋር በአፍ መላፋት የምወደው ልጅ ተዘግቼ ወጥቼ ተዘግቼ የምገባ ሆንኩ፡፡ የማየው ነገር ሁላ ምንም አልጥምህ አለኝ፡፡ ቀጥ ያለ እንቅልፍ መተኛት አልቻልኩም፡፡ ከተኛሁ*

> እስኪነጋ ቢያንስ ሶስቴ እባንናለሁ። አንዳንዴ ድንጉጥ፣ እጅግ ጠንቃቃ እሆንና ከዛ ብሞትም ግድ የማይሰጠኝ ሰው እሆናለሁ (138-39)።

እዚህ ትረካ ውስጥ የአላዛርን የትራውማ ታማሚነት የሚያመላክቱ በርካታ ምልክቶችን እናገኛለን። የሚፈልገውን መሆን ተስኖታል። በብቸኝነትና በዝምታ ተውጦ ከእኩዮቹ ተነጥሏል። ለሚያየው ነገር ስሜት አልባ ሆኗል። እንቅልፉ ጤናማ ካለመሆኑም በላይ በበዛ ድንጉጥነትና ጠንቃቃነት ተውጧል።

የአላዛር የስሜትና የባሕርይ ለውጦች በዚህ ብቻ የሚያበቁ አይደሉም። ጠጪ፣ ሴት ጎንታይና ካገኛት ጋር አዳሪ ይሆናል። አቶ መክብብን ለገደሉ ሰዎች ራሱን ተባባሪ አድርጎ በመቁጠር ራሱን ይወቅሳል፤ ገዳዮቹን ይወቅሳል፤ መንደርተኛውን ይኮንናል። ከአብሮ አደግ ጓደኞቹ ጋር ያለው ግንኙነት በጥርጣሬ ይሸበባል። በወቅታዊው ሁኔታ ስጋት የገባቸው ወላጆቹ ከአገር ወጥቶ ወደ ጀርመን እንዲያመራ ሲያደርጉት ከእነሱ ጋር ያለውን ግንኙነት ሳይቀር ይቆርጣል። ያለ እሱ መተንፈስ አይችሉም የሚባሉት እናቱ እሱን በማጣት እንደተጎዱ ጓደኞቹ እየጻፉለት ለእሳቸው እንኳን ምላሽ መስጠት ይሳነዋል። የውጭ ሀገር ኑሮውን ሙሉ ማለት ይቻላል ስለ ትላንት ገጠመኝና ሕይወቱ ትርጉም በመፈለግ ተጠምዶ ነው የምናየው።

ከአላዛር ባልተናነሰ የትራውማ መንስኤና ውጤት በጉልህ የሚታይባት ገጸ ባሕርይ ተባረኪ ናት። ተባረኪ በብርቱ ተማሪነቷ መንደርተኛው ምሳሌ የሚያደርጋት ልጅ ነበረች። ድንገት ግን በፖለቲካ ተሳትፎዋ ስትዋጥ በምሳሌነት ለሚያነሳት መንደርተኛም ሆነ ከምንም በላይ ለሚወዷት እናትና ፍቅረኛዋ (አላዛር) ግድ የሌላት ትሆናለች። የዘወትር ሩጫዋ፣ የዘወትር ቋንቋዋ 'ድርጅት' 'ድርጅት' ወደምትለው ፖለቲካዊ ተግባሯ ብቻ ሲሆን ከአላዛር ጋር የሚገናኙበት፤ ሲገናኙም የሚግባቡበት ሁኔታ ይጠፋል። በመጨረሻዋ የመስነባበቻ ቀናቸው ሳይቀር መግባባት ሳይችሉና ቅራኔያቸውን ሳይፈቱ አላዛር ተለይቷት ይሄዳል።

በአንዱ እለት በሰፈሯ አብዮት ጠባቂና የራሷ ድርጅት አባል እንደሆኑ በጠረጠረቻቸው ልጆች የቤቷ በር ተንኳኩቶ መሳሪያ ተደቅኖባት ወደ እስር ትወሰዳለች። አላዛር ታስሮበት በነበረ በላብና በሽንት ጠረን በተበከለ ክፍል ውስጥ ታስራ በተደጋጋሚ በአፍዋ ጨርቅ እየተጎሰጎሰ ተገልብጣ ትገረፋለች፤ ለህሊና በሚከብድ መንገድ ትደበደባለች። ድብደባው ብቻ ሳይሆን ጎረቤቴና የትግል አጋሮቼ የምትላቸው ሰዎች በጉዳቷ ተሳታፊ መሆናቸው የማትጠብቀው መከዳት ሆኖባት ግራ ትጋባለች። እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ለትራውማ ምክንያት የመሆን ኃይል አላቸውና በቅዠትና በቀን ህልም መናወዝ የምትጀምረው እዛው እስር ቤት ውስጥ ነው፤

> [. . . ] ሰይጣን ከነፍሴ ጋር እንቁልጭልጭ የያዘ ይመስለኛል። [. . . ] አንዳንዴ ፈረንጅ አገር እሄዳለሁ። በማላውቀው ትልቅ ፎቃም ከተማ ውስጥ አላዛርን እፈልገዋለሁ። ፈጣን ባቡሮች በሚንካኩበት፣ ባዕድ ቋንቋ በሚተረተሩ ሰዎች መሃል፣ በትርምሱ፣ የሆነ አደባባይ ጥግ ዋሀድ ሽንኩራ ሲሸጥ አገኘዋለሁ። አያውቀኝም። ማን እንደሆንኩ ብነግረው አያውቀኝም። ባዶ ቤት ገብቼ አኩርፌ እቀመጣለሁ። አላዛርን እንደምጠብቅ ትዝ ይለኛል። የምጠብቀው አላዛርን ነው። ደሞ አልጠብቀውም። አለሁበት ክፍል ውስጥ ለሁለት ቀናት በወፌ ያገላበጠኝ ካድሬ በግ እየጎተተ ይገባል። ከክፍሉ እየሮጥኩ እወጣለሁ። 'በረት ውስጥ ምን ትሰሪያለሽ' ይለኛል። ወደ ውጭ እየሮጥኩ ስወጣ ደብረዘይት ከተማ ነው፣ መንገዶቹ በጋሪ ተሞልተዋል (271) ።

እንዲህ የጀመረው የልቡናዋ ሁከት ከእስር ተፈትታ ለትምህርት አዋሳ ከሄደች በኋላ በሚታዩ ተግባሮቿ ጭምር መገለጥ ይቀጥላል። "የአዋሳ ካምፓስ ዱርዬ" እስከመሰኘት ትደርሳለች። የወንድ ዐይነት ሳትመርጥ ለወሲብ ትሄዳለች። ለአደገችበትና ለኖረችበት ሰፈር ማኅበራዊ ግንኙነት ቦታ ታጣለች። ለአላዛር እናት ሞት ለቅሶ አለመድረሷ እንኳ ቅር የማያሰኛት ትሆናለች።

ከጊዜው ፖለቲካ ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ካላቸው መንስኤዎች በዘለለ ግለሰባዊ የሆኑ ምክንያቶችም ለትራውማ መንስኤ ሆነው ይገኛሉ። የዚህ ጥሩ ማሳያዋ ማክዳ ናት። ድህነት ውበቷን ያልሸፈነባት ይህች የ16 ዓመት ታዳጊ ማጣቷን ተገን ባደረገች የመንደሯ ባለ ቡና ቤት ሴት ተታላ ዕድሜው በገፋ ሀብታም ተገዳ ትደፈራለች። የድርጊቱን አፈጻጸም ኢ ሰብአዊነት ለማሳየት ያህል የሚከተለውን ልጥቀስ፤

> "ልጅ የለውትም ወይ!" "ሴት ልጅ የለውትም ወይ!" ምንም ነገር አላቆማቸውም። ብገለባበጥ፣ ብፍጨረጨር አይኖቻቸው ፈጠው ሊገሉኝ ደረሱ። የመገለባበጥ የመፍጨርጨር ልምድ የለኝም። ይሄ ችሎታ እንዳነሰኝ ሲገባኝ አለቀስኩ። እንደዛን እለት ለማንም ሰው ጮኬ አልተናገርኩም [...]

> በትልቅ እጃቸው ፊቴ ላይ አንዴ ሲያጮሉኝ፣ ቀና ካልኩበት አልጋ ላይ ራሴን ስቼ ተመልሼ ወደቅሁ […] (463)።

በአባት ወይም በአያት እድሜ ላይ ባለ ሰው በእንዲህ ዐይነት ጭካኔ የሚፈጸም መደፈር ለ16 ዓመት ልጅ ምን ያህል አስደንጋጭና አስፈሪ እንደሚሆን ግልጽ ነው። ከተቃራኒ ጾታ ጋር በፍቅር ስሜት መቀራረብን እንኳን ገና ያልጀመረች ልጃገረድ የነተበ ቀሚሷን፣ ያለቀ ጫማዋን እንድትቀይር ባደረጓትና ጥሩና ደግ ናቸው ብላ በተቀበለቻቸው ሰዎች (አልማዜን ጨምሮ) ለዚህ መዳረጓ በሰው ላይ ያላትን እምነትና ተስፋ፣ ለዓለም ያላትን በጎ አመለካከት የሚያጨልም ነው። ከዚያ በኋላ ውበቷን ተጠቅማ ከተለያዩ ወንዶች ጋር ወሲብ መፈጸምና ገንዘብ ማግኘትን ስራዬ ብላ ትቀጥላለች። ይህ ተግባሯ ከHerman "የትራውማ ተጎጂዎች ለምን እንደሚያደርጉት ሳያውቁ ለትራውማ የዳረጋቸው ሁነት አካል በሆነ ተግባር ሲጠመዱ ይስተዋላሉ" የሚል ሐሳብ ጋር በቀጥታ መያያዝ የሚችል ነው (2015: 40)። ማክዳ ከተደፈረች በኋላ ወንዶችን በወሲብ የማዳረስ አመል ማምጣቷ የትራውማው ግፊት እንደሆነ ማሰብ ይቻላል።

በገጸ ባሕርያቱ ስሜትና ድርጊቶች እንዲህ መታየት የጀመረው የትራውማ አዋኪነት በቀጣይ ሕይወታቸው ውስጥም በተለያየ መንገድ ሲገለጥ ይታያል።

## ትራውማና የማንነት ቀውስ

Caruth የትራውማን ምስቅልቅል የሚፈጥረው ገጠመኙ ራሱ ሳይሆን ትውስታው መሆኑን ያስገነዝባሉ (1995፡ 17)። በተጋልጦው ወቅትም ሆነ በኋላ ተጎጂው የሆነውን ተገንዝቦ ስሜቱን በመግለጽ እረፍት አያገኝም። ከዚያ ይልቅ ከድንገተኛ ስሜቱ ጋር በሚደረግ የላፍንህ አልታፈንም ትግል ይጠመዳል። ሆኖም ብዙ ጊዜ ትራውማዊ ስሜቶችን ማመቁ አይሳካም። ይልቁንም ከቁጥጥር ውጭ በሆነ መንገድ በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ መልካም ባልሆነ መንገድ እየተገለጸ ይመጣል። በተለያዩ ውጫዊ ሁኔታዎችና ተግባሮች ሲገለጹ የሚታዩት የትራውማ ምልክቶች የውስጣዊ ትግሉ (ልቡና) መገለጫዎች ናቸው። የትግሉ መክፋት የልቡናን ሚዛን የማዛባት ኃይል አለው። የልቡና ሚዛን አንዴ በትራውማ ከተዛባ ጉዳዩ ያለፈ ብቻ ሆኖ የሚቀር አይሆንም። Eyerman እንደሚለው የዛሬ ወይም የአሁን ጉዳይ ይሆንና ማንነትን ይጎዳል፤ "Trauma links past to recent through representations and imaginations. In psychological accounts, this can lead to a distorted identity-formation, [. . .]" (2001፡ 3)።

በወጥ እኔነት መዝለቅ (self-sameness and continuity) መቻል ከማንነት መገለጫ ባሕርያት ዋነኛው ነው። ሆኖም ትራውማ ይህ እንዲሆን አይፈቅድም። ተጎጂዎቹ ለትራውማ ከተጋለጡ በኋላ የዘወትሩን ማንነታቸውን ያጡታል። ስለ ራሳቸው የነበራቸው ግምት ይወርዳል፤ ባዶነትና ተስፋ ቢስነት ይውጣቸዋል፤ ከሌሎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ይበላሻል ወይም ይቋረጣል፤ ለማኅበራዊ ወግና ልማዶች ዋጋ ያጣሉ፤ ብቸኛና ባይተዋር ይሆናሉ፤ ወዘተ። ትራውማ ሥነ ልቡናዊ የማንነት መዋቅርን ብቻ የሚያውክ አይደለም። ግለሰብንና ማህበረሰብን የሚያስተሳስረውን የግንኙነት ሥርአት ጭምር የመጉዳት ኃይል አለው። "Traumatic events have primarily effects not only on the psychological structures of the self but also on the systems of attachment and meaning that link individual and community" (Herman 2015: 51)።

ከመረቅ ውስጥ ለዚህ ማስረጃ የሚሆኑ በርካታ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል። እዝራ፣ ማክዳ፣ ተባረኪም ሆነች አላዛር በቀደመ የእነሱ ባሕርያት ላይ አይገኙም። የተፈጠረባቸው ትራውማ ወጥ እኔነታቸው እንዳይዘልቅ በማድረጉ ከቤተሰቦቻቸው ጀምረው ቅርቦቻቸው ከነበሩ ሰዎች መራቅ፣ ማኅበረሰቡ ባነወራቸው ተግባራት ላይ መዋል (ለማኅበረሰቡ እምነትና ልማድ ግዴለሽ መሆን)፣ ሀዘኔታ ማጣት፣ ወዘተ ዐይነት የእነሱ ያልነበሩ ባሕርያትና ስሜቶች የሚነግሱባቸው ናቸው። የእነሱ ማንነት መገለጫ ባልሆኑ አስነዋሪ ሁኔታዎች ላይ በመገኘታቸው መልሰው ከራሳቸው ይጣላሉ። ማክዳ ለትራውማ ከተጋለጠች በኋላ እንደ መጽናኛም እንደ መበቀያም ከወንዶች ጋር በወሲብ ቆይታ ቤቷ ስትገባ፤ አልያም እዛው ከአልጋው ሳትነሳ በሚሰማት ስሜት ምን ያህል ከራሷ እንደምትጣላ ማየት ይቻላል (469-470)። ራሷን በዚያ ዐይነት

ተግባር ላይ በማግኘቷ ደስታ አይሰማትም፡፡ ግን ደግሞ መልሳ እዛው ናት፡፡ ግራ ተጋብታለች፡፡ በምታስበውና በምታደርገው መኃል ልዩነት አለ፡፡ የምታደርገው የምታምነውን አይደለም፡፡ ይህን ስታገናዝብ ደግሞ ከንቱነትና ቆሻሻነት ይሰማታል፡፡ ራሷን በደደብነት እስከመፈረጅ ደርሳለች፤ በገዛ ራሷ ፍረጃ ራሷ መልሶ እስኪያሳዝናት ድረስ አይረቤነቷን አምና ተቀብላለች፡፡ ራሷን ወቅሳለች፡፡ ለራሷ ያላት ግምት መውደቅን እሷ ስለ ራሷ በምታስበው ብቻ ሳይሆን ወደ አልጋ በሚጎትቷት ዓይነተ ብዙ ወንዶች ውስጥ ጭምር ታየዋለች፡፡

> […] በልቤ ገብቶ ትንሽነት የሰጠኝ ታሪኬ፡፡ […] መዝነውኝ የቀረቡኝ ይመስለኛል፡፡ ሚዛኑ ላይ ሀፍረትና ትንሽነት ይቀመጥና ከዛ ዝቅተኝነትና ቂልነት ተደባልቆ እንደ ጨው ከላዩ ይነሰነስበታል፡፡ 'ማንም የተጫወተባት' ሆኜ ነው የሚያገኙኝ፡፡ የተሰናዳሁ ነኝ፡፡ የምደረገው እኔ ብቻ አይደለሁም ታሪኬም ነው (480)፡፡

በራስም በሌሎችም ሚዛን ከክብርና ከግምት በታች መሆኗ ተያይዘው በሚመጡ የሐፍረት እና የጥፋተኝነት ስሜት ይታጀባል፡፡ እናም ከገዛ ቤተሰቦቿ ጭምር ትሸሻለች፡፡ እንደ እዝራ በፍቅርና በክብር ሊያቀርቧት ሲሞክሩ እንኳን ጥሩ ስሜት አይሰማትም፤ "ለምንድን---ሽርሙጣ ነሽ' ብለው ከማያከብሩኝ፣ የሚያከብሩኝን ሽሺ ሽሺ የሚለኝ?" (519) ነው የምትለው፡፡ ትጠይቃለች እንጂ መልስ የላትም፡፡ ለራሷ ያላት ግምትና ክብር ባዶ በመሆኑ ክብሩ ያልተገባ እየሆነባት ያሳቅቃታል እንጂ ምክንያቱ አይገለጥላትም፡፡ ለራሷ ያላት ግምት ከመበላሸቱ የተነሳ ከሌሎች ጋር ያላት ግንኙነት ጭምር ነው የሚታወከው፡፡ ከራሷ ብቻ ሳይሆን ከማኅበረሰቡ ዘንድ ባላት እይታም ነው የማንነቷ ምስል የሚረክሰው፡፡

ለዓላማዋ ታጋይና ጽኑ የነበረችው ተባረኪ ባላቀደችው አመጣጥና አጨራረስ ላይ በመገኘቷ፣ ያለችበትንም በምርጫ ሳይሆን በግድ በመኖሯ ጉዞዋን ከቁልቁለት የምታመሳስል ሆናለች፡፡ በአንጻራዊነት በተሻለ የክብርና የኑሮ ደረጃ ላይ ሆናም ራሷን ከሌላ ጋር በማወዳደር ዝቅተኝነት ይሰማታል፡፡ ዛሬዋን ከግብ ካልደረሰው የግል ህልሟ ጋር አነጻጽራ የምትደርሰው ማነስ ላይ ብቻ ነው (306)፡፡ አግብታ ወልዳ እየኖረችም ዛሬዋ ጎዶሎነቱ እንጂ ሙሉነቱ አይሰማትም፡፡ ግን ደግሞ ይሄን ለመቀየር የሚያስብና የሚያስችል ወኔና ጽናትም አልተረፋትም፡፡ እንዲሁ ያለፈውን እያሰበች በመዋል ትደክማለች እንጂ ዛሬዋን በትክክል እየኖረች አይደለም፡፡ ከባሏ ጋር በምትፈጽመው የሥጋ ተራክቦ ውስጥ ሳይቀር ከቀደመ ወዳጇ (ከአላዛር) ትውስታ ጋር ትታገላለች፡፡ በእስር ቤት ስትገረፍ አንዱ ገራፊ በደም በራሰ ጣቱ የነካውን የጭኗን ክፍል ገላዋን በታጠበች ቁጥር እየፈገፈገች አለች፡፡ ትላንቷ ከዛሬዋ ከመቀላቀሉ ብዛት ዛሬዋ በትላንቷ ትውስታ ይታወካል፡፡ ጸጸት አለባት፡፡ ፖለቲካ ፖለቲካዋን ስትል የሚወዷትን ሰዎች ቸል በማለቷና በማስከፋቷ፣ ለግል ሕይወቷ ሳታስብ ብዙ የሆነችለት፣ ብዙዎች የተሰዉለት ዓላማ ሜዳ ወድቆ በመቅረቱ ዘወትር ትቆጫለች፡፡

በስደት ያለው አላዛር አካሉ እንጂ ሐሳቡ ሁሉ አገሩ ላይ በነበረው የትላንት ትውስታው ውስጥ የሚዋኝ ነው፡፡ መልካም የነበሩትንም የከፉትንም ትውስታዎቹን ነው መልሶ መላልሶ የሚኖራቸው ማለት ይቻላል፡፡ ባለፉት ነገሮች ራሱንም ሌሎችንም ይወቅሳል፣ ይተቻል፣ ይጠይቃል፡፡ እንደዚያ ክንፉን ዘርግቶ የበረረለትን የተባረኪ ፍቅርና የፍቅረኛውን ማንነት ሁሉ ወደ ኋላ ተመልሶ ጠያቂና መዛኝ ይሆናል፡፡ ከተባረኪ ልጅ መውለዱን ላበሰረው ዜና ስሜት ከማጣትና ልጁን መቀበል ካለመቻሉ ጀምሮ አገር ቤት ካሉ ቤተሰቦቹና ጓደኞቹ ጋር የነበረው ግንኙነት ላልቶ ይቋረጣል፡፡ ዋጋ ካለው የጓደኝነት እና የግንኙነት ምስል፣ ከጠበቀ መቀራረብና አብሮነት ተነጥሏልና መኖሩ ዋጋ አጥቶበታል፡፡

ትላንቱ እንጂ ዛሬው ስሜት የሚሰጠው ሊሆንለት አልቻለም፡፡ የአብሮ አደጉን የፀናፅልን ጥሪ ተቀብሎ ወደ አሜሪካ ከሄደና ካገኛት በኋላም ስሜቷን የሚጋራበትና የሚቀበልበት አቅም ያጣል፡፡ ፀናፅል ከልጅነቷ ጀምራ አፍና የኖረችውን ፍቅሯን፣ ሰው አገር በስደት ያቆየችውን ድንግልናዋን እንዲጋራት እየነገረችው እንኳን የሚሸነፍ ልብና ለዚያ የሚሆን ስፍራ አይኖረውም፡፡ እንዲያ ለሴት ገላና ለፍቅር ግንኙነት ንቁ የነበረ ሰው፣ እሱን ብላ ብዙዎች በማይሆኑት መንገድ በፍቅርና በናፍቆት የተጎዳች ልጅ ከጎኑ ሆና ለጉጉቷና ለጥያቄዋ ምላሽ መስጠት ያቅተዋል፡፡ ተለውጧል፡፡ ራሱም እስኪገባውና እስኪናገረው ድረስ ሌላ

ሰው ሆኗል፤ “ፀናፅል ድሮ የምታውቀኝ ልጅ አይደለሁም። ሁለመናዬ ተለውጧል። የሆነ ጉም ከቦኝ የሚሄድ ይመስለኛል። ጭማቂዬ በአጭር ጊዜ በዕድሜና በኑሮ እንደ ከረመ ጠላ ኮምጥጧል። እሷ ስትወደኝ የነበርኩት አላዛርና አሁን አንድ አይደለሁም” (189)።

እነ አልማዜን፣ አላዛርን በእስር ቤት የሚመረምረውን ወታደር፣ ሌሎችንም ብንወስድ ለትራውማ ከመጋለጣቸው በፊትና በኋላ የነበራቸውን የስሜት፣ የአስተሳሰብ፣ የአቋም ልዩነት በማነጻጸር የአንድ ሰው ማንነት በትራውማ አማካይነት ምን ያህል እንደሚታወክና እንደሚቀየር ማስተዋል ይቻላል። የመረቅ አብዛኛዎቹ ገጸ ባሕርያት አካላዊ እና ሥነ ምግባራዊ በሆኑ ጥቃቶች ለትራውማ የተጋለጡ ናቸው። እንደህ ባለ ባለ ሁለት ስለት ጥቃት የሚፈጠር ትራውማ ጉዳቱ ይከፋል። የZepinicን “Two interconnected inescapable traumatic experiences (physical and moral violation) destroy the individual’s capacity for a flourishing life of any kind, at anytime and anywhere” (2012: 280) ሐሳብ ብንመረኮዝ የግለሰብ ሕይወት ጽልመት መልበሱን፣ ወደ ተሻለ ደረጃ የመድረስ ጉዞ መደናቀፉን መገንዘብ ይቻላል። መረቅ ውስጥስ ሕይወቱ አብቦ ራሱን በደስታና በእርካታ፣ ተመልካቹን በአድናቆትና በይሁንታ ያስደመመ ማን አለ? አላዛር በስደት ከዛሬው መሆን እያቃተው ከትላንት ትውስታው በመታገል ደፋ ቀና ላይ ነው። ተባረኪም ቤት ትዳር ልጅ ይዛ ትላንትን ይሁን ዛሬን የምትኖረው ግራ እንደገባት ናት። ማክዳ የተጣመመውን መስመሯን አቃናሁ፣ ወደ ፊት ተራመድኩ ስትል ከትላንት ሕይወቷ የሚመዘዘው እክል አልለቅ ብሏት ባለችበት ትዳክራለች። እዝራ ችግሬን አሸነፍኩ፣ ምኞቴን አሳካሁ ሲል ደርሶ ቆስቋሽ ነገር፣ የጨበጠውን የሚነጥቅ ነፋስ አልጣህ ብሎት በቀልና ግዴለሽነት ውጦታል። ሁሉም እንኳን ስለመጪ ጊዜያቸው ሊያስቡና ሊያበጁ ያሉበትንም ዛሬ ማቅናት ተስኗቸዋል።

የገጸ ባሕርያቱ ትራውማዊ ገጠመኞችና ቀውሶች በሚኖሩበት ማኅበረሰብ ወይም ባህላዊ አውድ ውስጥ የሚከናወኑ በመሆናቸው ግለሰባዊ ብቻ ሆነው ሊቀሩ የሚችሉ አይደሉም። የሚከተለው የBell ሐሳብ ይህንኑ ያጠናክራል፤ “[T]rauma can never be a purely individual event, in the same way as there cannot be a private language, because it always already involves the community or the cultural setting in which people are placed” (2006: 107)። አባላቱን በነጠላ ከሚገጥማቸውም ሆነ በወል ከሚፈጠር ሁኔታ የሚመነጨው ትራውማ ጉዳት ዞሮ ዞሮ ማኅበረሰብን መንካቱ አይቀርም።

በመረቅ ውስጥ ከግለሰብ ያለፉ የትራውማ ጉዳቶችን የሚያመላክቱ የማኅበራዊ ግንኙነቶች መቋረጥ እንዲሁም ወግና ልማዶች መጣስ እናያለን። በጥብቅ ግንኙነት፣ በክፉና በደግ የመደራረስ ልምድ የተገነባ የነበረው የማኅበረሰቡ ማንነት እየተለወጠ ሄዷል። በተፈጠሩት አደገኛና ውስብስብ ነገሮች የእርስ በርስ መተማመኑ ጠፍቷል። አላዛር ለጓደኛው አባት ሞት ፀጉሩን ተላጭቶ፣ ጥቁር ለብሶ እንዳላዘነ፤ የቤታቸውን በር ቢቆረቁር የማይከፍቱለት፣ ቢጠራቸው መልስ የማይሰጡት ሆነውበታል። ጥርጣሬ፣ መፈራራት፣ መወነጃጀል ወሯቸዋል። ያስተሳሰራቸው የፍቅር ሰንሰለት ተበጥሷል። ይህን ሁነት ተባረኪ እንዲህ ትገልጸዋለች “በስንቶቻችን መኃል ሽብልቅ ገባ? በእኔና በአላዛር፣ በእኔና በእማማ፣ በእማማና በአላዛር ቤተሰብ […]” (277)።

አላዛር፣ እዝራ፣ ተባረኪ ለወላጆቻቸው ብቸኛ ልጆች ናቸው። ማኅበረሰቡ እነዚሁ ልጆቹ ናቸው በእስር፣ በግርፊያና በውክብያ ተደናግጠው፣ በፍርሃት ተሳቀው በየአቅጣጫው ተበትነውበት የሚያጣቸው። የቀሩትና አጠገቡ ያሉትም በመጠጥና በወሲብ ቀንና ሌሊታቸውን የሚገጥሙ ለመሆን በቅተዋል። እዝራ ከሆቴል ቤቱ ከሚያየው ተነስቶ የሚሰጠው ምስክርነት ይሄን ያረጋግጣል።

> በወጣቶች ደጋግሞ መምጣት የሆቴሌ አልጋዎች ሽቦ መርገብ ጀመረ የበሮቹ ማጠፊያ ምስማር ላላ። ተኩሰው ያገኙ፣ ተኩሰው የሳቱ፣ ተተኩሶባቸው ያመለጡ ግን የተበተኑ ጎረምሶችና ኮረዶች ብቅ አሉና ሆቴሌን በ‘እንዝናና’ ናጧት […] አልኮል መጠጣት ያሳፍረው የነበረ ጉብል በአጭር ጊዜ ነፍሱ አርጅቶ ጂን መምጠጥ ጀመረ። […] ጠዋት ላይ ከሆቴሌ ፊት ለፊት፣ ከመንገዱ ወዲህ

> ሁለት ሶስት ሰው ማስታወኩን የሚያሳዩ ምልክቶች ብቅ ማለታቸው ደንብ ሆነ። ፀጥታ ሰፍኖበት የነበረው ሰፈሬ ንጭንጭ ያለ ጩኸት ወረረው [...] (392)፡፡

የመተኪያ የለሾቹን ብቸኛ ልጆች ተበትናና ባክኖ መቅረት ከአገር ያለተተኪ ትውልድ (ጤነኛ ሥነ ልቡና ያለው) መቅረት ጋር ማናበብም ይቻላል፡፡

እነ ማክዳ፣ አላዛር… እንደ ግለሰብ ግላዊ ገጠመኝና ቁስል ቢኖራቸውም የማኅበረሰቡም አካል ናቸውና ቁስልና ጉዳታቸው የማኅበረሰቡም ነው፡፡ በእርግጥ በወል ትራውማ የማኅበረሰቡ አባል ሁሉ በአንድ ጊዜ አንድ ዐይነት የትራውማ ምልክት እንዲያሳይ አይጠበቅም፡፡ በግለሰብ አባላቱ አማካኝነት መገለጫው የሆነ እምነት ባህሉ ሲሸረሸር፣ አቋሙ ሲላላ፣ ኩራት ክብሩ ሲወርድ ይታያል እንጂ፡፡ እንደ Eyerman ሐሳብ ይህ የባህል ትራውማ (cultural trauma) መገለጫ ነው (2001፡ 2)፡፡

ማኅበረሰቡ 'ነኝ' ወይም 'መሆን ይገባል' ከሚለው በተቃራኒ ሆኖ ሲገኝ ምን ሆኗል? ተብሎ ሊጠየቅ ይገባል፡፡ በርግጥ ምን ሆኗል? የመረቅን ማኅበረሰብ አቋሙን የሚጎዳ፣ የአባላቱን መለያ ባሕርይ የሚያውክ ምን ገጥሞታል? ብለን ብንጠይቅ ሩቅ የማያስኬደው ምላሽ ወቅቱ እንዲጋፈጥ ካደረገው ምስቅልቅል የሚርቅ አይሆንም፡፡ እምነቱም እውቀቱም የማይደግፍና የማይፈቅደውን ተግባር በድብቅ የሚፈጽምበት፤ በሚያነውረው ድርጊት ውስጥ መልሶ ራሱን የሚከትበት፤ ያልተገነዘበውና ከቁጥጥሩ ውጭ ሆኖ የሚገፋው ድብቅ ሕማም ቢኖር ነው ብሎ ለማሰብ የሚከብድ አይሆንም፡፡

የመረቅ አውድ እንደሚያሳየን ከቀደሙ ጊዜያት (የጣልያን ወረራ) አንስቶ ሲጠራቀም የመጣ የልቡና መታወክ አለ፡፡ በዚህ የተነሳ የማኅበሩ አቋም እና መገለጫ ባሕርይ ፈርሶ ይታያል፡፡ የሚከተለው የአላዛር ገለጻ ይህን በሚገባ ማሳየት የሚችል ይመስለኛል፤ "ወደ ተዘባረቀ ወደ ደፈረሰ በተገኘው መንገድ መናከሻ በሚፈልግ አካሄዱን ወደማያውቅ መጋጋጥ ባህሉ እንዲሆን ወደ ተደረገ ኩሬ ተመልሼ አልገባም፡፡ አሳው ውሃውን እየበላ ነው " (184፤ አጽንኦቱ የእኔ ነው)፡፡ "አሳው ውሃውን እየበላ ነው"- የነዋሪው መኖሪያውን ማጥፋት ከባድ ሕማም ነው፡፡ ነዋሪውን ያለመኖሪያው ማሰብም የሚቻል አይደለምና መኖሪያውን እያጠፋ ያለን ፍጡር የመኖር ዘላቂነት ጥያቄ ውስጥ ያስገባል፡፡ የመረቅ ማኅበረሰብም እንደ ልምድና ተፈጥሮው የሚዋኝበትንና የሚኖርበትን ውሃውን (ማኅበራዊ እሴቶቹን) በትራውማ ምክንያት መልሶ እያጠፋና እያጣቸው አለ፡፡ ይህ ደግሞ ለታማሚነቱ እንጂ ለጤነኛነቱ ምስክር የሚሆን አይደለም፡፡

ከማኅበረሰቡ ታማሚነት የተነሳ የትኛውም ግለሰባዊ ትራውማ በማኅበረሰቡ ልማድና አኗኗር አጋዥነት እንዲፈወስ ወይም እንዲበርድ ሲሆን አይታይም፡፡ ይልቅስ እንዲብስና እንዲጠነክር ሲሆን እንጂ፡፡ የተባረኪ አንዱ የእስር ቤት ገራፊ ደም በነካቸው ጣቶቹ የነካትን ከግራ ጭኗ ውስጥ ያለች ቦታ ዘወትር የተነከሰች ያህል እስኪቀላ ፈቅፍቃ መታጠብ (268)፣ የማክዳ ድብርትና ናፍቆት ባየሉባት የመጨረሻዎቹ ጊዜያት ላይ ያመጣችው ደጋግሞ ገላና አፍረትን መታጠብ (554) የልቡናቸው የፈውስ መሻት ምልክት ይመስላሉ፡፡ ሆኖም የማኅበረሰቡ ራሱ በጤና አለመገኘት እነሱን ወደ ፈውስ ከመምራትና ከማገዝ ይልቅ ሕመማቸውን የሚያባብስ ነው የሚሆንባቸው፡፡

በመረቅ ውስጥ የማኅበረሰብን ልማድና አኗኗር እስከመቀየር ደርሶ የሚታየው ትራውማ አዋቂዎቹን በጥርጣሬና በፍርሃት ተይዘው እርስ በርስ የማይጨዋወቱ አድርጓቸዋል፡፡ የቤተሰብ ያህል የሚቀራረቡና የሚተሳሰቡትን ወጣቶች አራርቆ፤ መንደር ቤታቸውን (አገራቸውን) ጥለው የሚሰደዱ፣ ለወዳጅ ባልንጀሮቻቸው ሞትና ሀዘን የማይደርሱ፣ የልጅነት መንደራቸውንና ሰዎቹን ባያዩ ባያገኙ የሚመርጡ አድርጎ ሰርቷቸዋል፡፡ እንደልባቸው ተናግረው በማያወጧቸው ጭንቀቶችና ስጋቶች በመሞላታቸው ባልተገቡ የወሲብ ተግባራት ይጠመዳሉ፡፡ ሴተኛ አዳሪና ባለ ቡና ቤቷ አልማዜ ወንዶቹን በወሲብና በመጠጥ ከማንበርከክ፣ ወጣት ሴቶቹን ለወሲብ ከመሸጥ ሌላ ከበሉበት ትሪ መረቅ ላይ ያረፈ የጣት ዳናቸውን በማንበብና ነጋቸውን በመጠንቆል ተቆጣጥራቸዋለች፡፡ በአደባባይ ብትናቅም 'አልማዜ' እየተባለች በቁልምጫ የምትጠራ ናት፡፡ ይህ እየገፋ መጎተት (እያንቋሸሹ ማቆላመጥ) የማኅበረሰቡን የአደባባይ እምነትና አቋም ከተግባራዊ አኗኗሩ ጋር የመለያየት (መቃረን) ጥሩ ማሳያ ነው፡፡ አልማዜ ብትናቅም

ብትገፋም በጥንቆላዋ፣ በጭኗ ደግሞም በገንዘብና በማባበል ችሎታዋ ተገፎዋ እንዲሆኑ አድርጋለች። የማኅበረሰቡ አባላት ባይፈቅዱም እየታዘዟት ነው። የልቡና ቁስላቸው መብዛት ለእሷ ዐይነት ወግና ልማዳቸውን ጣሽ ተንበርካኪ አድንቸዋል። ፊት ለፊት እየተጸየፉና እያንቋሸሿት ደግሞ በጓዳ፣ በጀርባ ከአልጋና ከጭኗ መሃል ይገኛሉ። አባትየው ባይሄድ ልጅየው በስሯ ነው (አላዛር)። አባትን በቤቷ አልጋ እያስተናገደች ሴት ልጁን ለሽያጭ ታቀርባለች (ማክዳ)።

ማክዳ ቡና ለመጠጣት ቤታቸው የመጡ የሰፈሯን እናቶች በምትገልጽበት የሚከተለው ንግግር የማህበረሰቡን ታማሚነት ማጽናት ይቻላል፤ " […] የሁሉም ሴቶች ነጠላዎቻቸው ከጥለታቸው የተዘነተሩ ናቸው። እያጣፉ ቀዳዳውን ይሸፍናሉ" (503፤ አጽንኦቱ የእኔ ነው)። ገለጻው ድህነታቸውን ከመንገር በላይ ይመስላል። በተለይ የሁሉም ሴቶች ነጠላ እንደዚያ መሆኑ የጋራ የሆነ ጉዳትን አመላካች እንደሆነ ማሰብ ይቻላል። እዚህ ንግግር ውስጥ የማኅበረሰቡ በየጊዜው በሚገጥሙት አገራዊና መንግስታዊ ውጥንቅጦች ለትራውማ መጋለጥ አለ። በውጭ ኃይል ወረራ፣ በእርስ በርስ ግጭቶች፣ በመልካም አስተዳደርና ፍትህ እጦት እየተንገላታ ከመምጣቱ ባለፈ የልጁን ወይ የጎረቤቱን ሬሳ እንደዋዛ ከመንገድ ዳር የሚለቅም እስከመሆን የደረሰ ነው። ለሀዘንም ለደስታውም የሚከናነበው፣ መለያ መገለጫው የሆነው ነጠላው ከጥለቱ ተዘንጥሎ መታየቱ ደስታና ውበቱን የማጣቱ ምልክት መሆን ይችላል። ባለ ህብረ ቀለሙ ጥለት፣ የነጠላው ጌጥ (ደስታው) እየተዘነተረበት እንዳይጠግነውም እንዳይቀይረውም አቅም አጥሮት፣ መላው ጠፍቶት ለብሶት ይኖራል። ተጎድቶ እንዳልተጎዳ፣ ቆስሎ እንዳልቆሰለ ቀዳዳውን ሸፍኖ ለመኖር የሚሞክር ማኅበረሰብ።

## የትራውማ ተሻጋሪነት

Caruth የታሪክና የትራውማን መመሳሰል በጠቀሙበት ሐሳባቸው እንደሚሉት አንዳችን በሌላችን ትራውማ ውስጥ አለን (1995፡ 24)። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ለአንዱ ታማሚነት የሌሎች ሚና ይኖራል። ይህም ነው ትራውማን በአንድ ሰው ብቻ የማይቆም ሰንሰለታማ ትስስር እንዲኖረው ያደረገው። በመረቅ ውስጥ በሥርዓቱ ተከልለው አሳሪና ገራፊ የሆኑትን ገጸ ባሕርያት ጨምሮ በፖለቲካውም በማኅበራዊ ኑሮውም ትራውማ በመፍጠር ሂደት ውስጥ ሚና ያላቸውን ሰዎች ለምን እንደዚህ ሆኑ ብለን ብንጠይቅ የምናገኘው ምላሽ ትላንት ሌሎች ካደረሱባቸው ጉዳት ርቆ አናገኘውም። ሁሉም የትላንት ጉዳታቸውን ዛሬ ሊበቀሉ የሚሞክሩ ናቸው ወይም በዚያ የሚገፉ ናቸው። ሆኖም በቀላቸው በዳያቸውን ለይቶ እሱ ላይ ብቻ የሚያርፍ አይደለምና ለሌላ ችግር ምክንያት ወደ መሆን ያልፋል።

አላዛር በእስር ላይ ሆኖ የሚያገኘው ካድሬ በአፄው ስርዓት የአባቱ አሳዳሪ በሆነ ጉልተኛ (ፊውዳል) በደል የልቡናም የአካልም ቁስል ያተረፈ ሰው ነው። የአካልና የህሊና ቁስሎቹን ይዞ 'ሁለት ጣት የሌለው' እየተባለ ሲጠራ አድጓል። የዚህ በደል ግፊት ወታደር አድርጎት ሲገኝ አጋጣሚውን መበቀያ ነው የሚያደርገው። ራሱም እንዲህ ይላል "የተቆረጡት ጣቶቼ ጠፉ? አልጠፉም። ልቤ ገቡና ጦር ሆነው በቀሉ" (125)። ደሃ አባቱን ጨምሮ በዳዩን ፊውዳልና ለፊውዳሉ የሚሰግዱለትን፣ የሚያከብሩትን ሰዎች ሁሉ ጠላ። ጥላቻው ገፍቶ ወስዶ ከውትድርና አስገብቶት ባለ ጦር መሳሪያና ባለ ኃይል አድርጎት ከአላዛር ጋር ሲገናኝ የሚናገረው የትላንት በቀሉን የመወጣት ጥሙን ነው። "መሳሪያ አለኝ። ጥላቻ አለኝ። ልጅነቴን ያበላሹብኝን ሲበላሽባቸው ምን እንደሚሰማቸው ማየት እፈልጋለሁ። ደስ እንደማይል አሳያቸዋለሁ" (126)። በተመሳሳይ የገዛ የሰፈሩን ልጅ (ተባረኪ) በር አንኳኩቶ፣ መሳሪያ ደቅኖ ለእስር የሚነዳው ወንደሰንም (የማክዳ አባት) ድህነቱና በድህነቱ ያሳለፋቸው የመናቅ ጊዜዎች ገፍተው አብዮት ጠባቂ ያደረጉት ሌላው በቀል የወለደው ሰው ነው።

ከትላንት ጉዳት (ትራውማ) የሚመነጨውን የተበቃይነት ስሜት ከግለሰብ ባለፈ መመልከት የምንችልበት ሁኔታም አለ። አልማዜ በመጠጥ ቤቷ ማስከሪያ አልኮልና የሴት ጭን በማቅረብ ኑሮዋን መመስረቷ፣ ህፃናትና ወጣቱን በድለላና በማማለል ወሲብ አለማማጅ መሆኗ፣ ገንዘብ ላላቸው ሽማግሌዎች ሴት

ህፃናትን ማቅረቧ በትላንት ሕይወቷ በወንዶች የደረሰባት በደል ግፊት ውጤት ነው፡፡ አንድ እሷ ላይ ያረፈ በትር ውሎ አድሮ ሰፊውን ማኅበረሰብ የሚደርስ ምላሽ ወልዷል፡፡ ራሷ፣ "...ወንድ አበጀኝ፣ ……ወንድ ተደባደበብኝ…" (86) እንደምትለው ያስርህራሄ በሰደዷት ጎዳና መልሳ ሌሎችን የምትሰድ ሆናለች፡፡

በትላንት ሕይወታቸው በተበደሉ ሰዎች ጥቃት የሚደርስባቸው የዛሬዎቹ ወጣትና ህፃናት መልሰው በተመሳሳይ መንገድና ስልት እንዳይሄዱ የሚያግድም የሚጠብቅም የላቸውም፡፡ የማክዳና የተባረኪ ወንዶችን በወሲብ የማጥመድ ሱስ ምንጩ ስለ ተቃራኒ ፆታ ግንኙነት ገና በቅጡ ማሰብና ማገናዘብ ሳይችሉ ጭኖቻቸው በወንዶች በመፈልቀቃቸው የተፈጠረና በልቡናቸው የታተመ ቁስል ነው፡፡ ከዚያም በላይ ብልግና እና ከንቱነታቸውን እያነሳ የሚጠቋቆምና የሚንሾካሾክባቸው እንጂ ምክንያታቸውን አጢኖ፣ ጉዳታቸውን ተረድቶ ስሜታቸውን ለመጠገን የሚሞክር አላገኙም፡፡ በዚህ አይነት ማኅበረሰብ ውስጥ መኖራቸው ለጉዳታቸው መቋቋሚ አቅም፣ ለሕመማቸው ማገገምያ እድል ያሳጣቸው ናቸው፡፡ ራሱ ማኅበረሰቡም በተደራራቢ የትራውማ ሕማም ውስጥ ያለ በመሆኑ የነጠላ አባላቱን ሕማም ተረድቶ ለፈውስ ሊያግዛቸው አልተቻለውም፡፡እንዲህ ለእያንዳንዱ የትራውማ መንስኤ ምክንያትና ውጤት እያበጀን በሄድን ቁጥር ማቆሚያ የሚገኝ  አይመስልም፡፡ የትላንቱ በደል የዛሬውን ጉዳት ፈጣሪ፣ የዛሬው ጉዳት ደግሞ የነገውን ጎጂ እየፈጠረ በመሄድ ሽግግሩ ይቀጥላል፡፡ ይሄ የትራውማ ከተጎጂነት ወደ ጉዳት ፈጣሪነት የመሸጋገር ሂደት የታወከው ልቡና ሲታከምና ሲፈወስ ብቻ ነው ሊገታ የሚችለው፡፡

ሌላው ዐይነት የትራውማ ሽግግር በቤተሰብ ውስጥ በሚኖር ታሪክ ነገራ አማካኝነት በትውልዶች መኃል ይካሄዳል፡፡[6] በመረቅ አያት ለልጅ ልጃቸው (አላዛርና አያቱ) በሚያደርጉት የዘመናቸው ሰቆቃና ፍጅት ትረካ አማካይነት የምናስተውለው የትራውማ ቅብብሎሽ Salter "Intergenerational trauma remains outside one's conscious understanding but can be accessed through symptomatic re-tellings of previous incidents of trauma with the family" (2012: 80) ሲሉ የገለጹት ነው፡፡ ተራኪዋ የሕማሙን መኖር ባይረዱትም በትረካቸው የምናስተውላቸው "እኛ አገር ከአመት አመት ጦርነት ነበር ልጄ፡፡ ስንቷ በሙሽርነቷ ቆማ ቀርታለች፣ እኔም አንዷ አይደለሁ፡፡ ስንቷ ባሏን፣ ስንቷ የከንፈር ወዳጇን አጥታለች፡፡ ቤት ይቁጠረው፡፡ ስንቱ ሎጋ አካለ ስንኩል ሆነ? [...]" (36) የሚሉ ገለጻዎቻቸው ሕመም ታቅፈው እንደኖሩ ያመላክታሉ፡፡ ይዘውት የኖሩትን ሕመም በጊዜውና በቦታው ላልነበረው ትውልድ በትራውማዊ ታሪክ ነገራቸው አማካይነት ያቃብሉታል፡፡ በዚህ መልኩ በቤተሰብ ውስጥ ባለ ታሪክ ነገራ ትራውማው ከትውልድ ወደ ትውልድ የመሻገር እድል አግኝቷል፡፡

## ትራውማን ያስተማስሉ ገጸ ጽሑፋዊ አቀራረቦችና ትዕምርቶች

የትራውማ ሥነ ጽሑፎች የልቡና መታወክ የሚነደፍባቸው በመሆናቸው እንግዳና ልማድ አፍራሽ አቀራረብ አያጣቸውም፡፡ ድግምግሞሽ፣ ቅደም ተከተሉ የተዛባ የታሪክ አቀራረብ፣ ያልተሟላ ክፍል፣ ግራ አጋቢ አቀራረብ፣ የተቆራረጠ ፍሰት፣ ያልተቋጨ  አጨራረስ፣ ወዘተ ደራስያን ትራውማን በሥነ ጽሑፍ ለመንደፍ ከሚገለገሉባቸው ዘዴዎች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ ስልቶች ከድህረ ዘመናዊ ሥነ ጽሑፍ ጋር የሚጋሯቸው ናቸው፡፡ Whitehead እንደሚሉት የትራውማ ንድፈ ሐሳብ መዳበር ለጸሐፍቱ ትራውማን በአዲስ እሳቤ እንዲያጤኑና ትውስታን የተመለከተ ጥያቄያቸውም 'ምን ታወሰ' ከሚል 'ለምን'ና 'እንዴት ታወሰ' ወደሚል እንዲቀየር አድርጓል፡፡ ሥነ ጽሑፉ ለእነዚህ የለምንና እንዴት ጥያቄዎች ከሕመሙ ባሕርያት በሚቀዱ የተለያዩ ስልቶች አማካይነት ምላሽ ያበጅላቸዋል፡፡ ትራውማን የማስተማሰያ ስልቶቹንም ትራውማ ከሚያስከትላቸው ተጽእኖዎች ያረቃቸዋል (2004፡ 3)፡፡

[6] በዚህ አይነት መንገድ ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍ የታሪካዊ ትራውማ ባሕርይ ነው፡፡ ብዙሃን ከገጠማቸው ትራውማዊ ሁነት የመነጨና የተጠራቀመ ሥነ ልቡናዊ ጉዳት ሲሆን ከረጅም ጊዜ በኋላም በትውልዶች መኃል መሸጋገር በመቻሉ ይለያል፡፡

የመረቅን የትረካ መንገድ ስንመለከት የትራውማን ዘግይቶ የመገለጥ ባሕርይ ሊያሳይ በሚችል መልኩ ያለፈን ሁነት ወደ ኋላ እያስታወሱ በመተረክ ስልት የቀረበ ነው፡፡ ገጸ ባሕርያቱ ሁኔታው ከገጠማቸው ጊዜና ስፍራ ርቀው በሌላ ጊዜና ስፍራ ላይ ሆነው ነው የሚተርኩት፡፡ ነገር ግን የጊዜና ስፍራ ድንበር ተጥሶ እዛው ጊዜና ስፍራ ላይ የሚሆኑበት ወይም ያንን ጊዜና ሁኔታ አሁን የሚያደርጉበት ይበዛል፡፡ ተራኪዎቹ ገጸ ባሕርያት (አሳዛር፣ ተባረኪ፣ እዝራ እና ማክዳ) ትረካቸውን በፊት እና በኋላ እያሉ የሚከፍሉበት የየራሳቸው የገጠመኝ ማዕከል አላቸው፡፡ ያ ማጣቀሻ ነጥባቸው (ማዕከላቸው) የትራውማ መንስኤ የሆናቸው አሰቃቂ አጋጣሚ የተፈጠረበት ጊዜና ሁኔታ ነው፡፡ ገጸ ባሕርያቱ ያዩትን፣ የሆኑትን፣ የሚያስቡና የሚሰማቸውን ቢሆንም የሚተርኩት መመርኮዣ እና ማንጸሪያቸው ያ ሁነት ነው፡፡ ትውስታቸው በፈቀደው መጠን ወደ ፊትም ወደ ኋላም እያሉ ቢያወጉንም የትውስታቸው ሁሉ ማጠንጠኛ ሥነ ልቡናዊ ቁስል የተዉባቸው ሁነቶች፣ ጊዜና ሥፍራዎች ናቸው፡፡ ከእነሱ ወጥተው ነገሮችን ማየት አይሆንላቸውም፡፡ እጅግ ተቆራኝተዋል፡፡ ከJanet በተዋስኩት ቀጣዩ ጥቅስ ይህን የትራውማ ታማሚዎች ከትራውማ ከሳቹ ሁነት ጋር አብዝቶ የመቆራኘት ሐሳብ ማጠንከር ይቻላል "…traumatized individuals become "attached"… to the trauma: unable to make sense out of the source of their terror, they develop difficulties in assimilating subsequent experiences as well" (በVan der Kolk እና Onno የተጠቀሰ፤ 1995፡ 164)፡፡ በዚህ አይነት የዚያን ጊዜው ገጠመኝ ትውስታቸው ያለፈውንና ያሉበትን ጊዜ የማገናኘት ሚና ጭምር እየተጫወተ ያስጉዘናል፡፡

የልቡና መታወክ የተለመደ የሚባለውን የነገሮችን ሥርዓት በማፋለስ ሊገለጥ ይችላል፡፡ በመረቅ ውስጥም ገጸ ባሕርያቱ በተለይ ለትራውማ ከተጋለጡ በኋላ የጊዜ ቅደም ተከተሎች ትላንት- ዛሬ- ነገ ወይም ቅድም- አሁን- በኋላ እየሆኑ አይመጡም፡፡ ገጸ ባሕርያቱ ያለፉበትን ሕይወት ሲተርኩልን ድንገት ካዩት ነገር ወይ ከተሰማቸው ስሜት ተነስተው ወደ ሆነ ጊዜና ቦታ ይወስዱናል እንጂ ለትረካቸው ተያያዥነትና ቀጣይነት አይጨነቁም፡፡ በተለይ ለትራውማ ያጋለጣቸው ሁነት ከተፈጠረ በኋላ ያሉት ትረካዎቻቸው፣ በቀደመው ትረካቸው ወቅት ባልነበሩ ቁልቁል የሚወርዱ ሶስት ነጥቦች (⁝) የተከፋፈሉ ናቸው፡፡ ቁልቁል ተቀማጮቹ ሶስቱ ነጥቦች ያያያዟቸውን ትረካዎች ስናስተውል በአብዛኛው አጫጭሮች (ቁርጥራጭ)፣ የቀደመው ከተከተለው ቀጥተኛ የሆነ የጊዜም ሆነ የምክንያት ውጤትና የተጠየቅ ዝምድና የማይታይባቸው ናቸው፡፡


በሐሳቦቹ እዚህም እዚያም መዝለል የሚገለጸው ኢ-ንቁው ልቡናቸው ነው፡፡ ኢ-ንቁው የልቡና ክፍል ከንቁው ልቡና በተለየ የሐሳቦች ተያያዥነትና ቀጣይነት ጉዳዩ ሆኖ አያስጨንቀውም (Easthope 2003፡ 5)፡፡ በውስጡ የታመቁ ስሜትና ሐሳቦችን እንዳሻው እንደመጣለት ነው የሚያወጣቸው፡፡ ይህ አካሄድ ያለ ተራኪ ጣልቃ ገብነት፣ ያለ የቅደም ተከተል ተዋረድ ጥያቄ በገጸ ባሕርያቱ አእምሮ ውስጥ ያሉ ሐሳቦችን፣ ስሜቶችንና ትውስታዎችን እንዳለ በማፍሰስ የሚታወቀው የእንደወረደ ስልት (Stream of consciousness)[7] መልክ መሆኑን ማስተዋል ይቻላል፡፡

ከትረካ መንገዱ በተጨማሪ በመረቅ ውስጥ ቁሶች፣ የመልክዓ ምድር ገጽታዎች፣ ንግግሮች፣ ድርጊቶች፣ ቅርጾች፣ ህልምና ቅዠቶች ለትራውማ ትዕምርት ሆነው ያገለግላሉ፡፡ በተለያየ ጊዜና ሁኔታ በገጸ ባሕርያቱ ሕይወት ውስጥ እየተገኙ ያረፉበትን፣ ያደሩበትን ትራውማና ጉዳቱን ያጎላሉ፡፡ ለሥነ ልቡና ጉዳታቸውና ትግላቸው ምስል ፈጥረው ረቂቁንና ውስብስቡን ሥነ ልቡናዊ ቁስል ተጨባጭ ያደርጋሉ፡፡ ለምሳሌ እንዲህ ሆኗል በመረቅ ፡- የመስመር ንድፎች የልቡናን እውነት አዝለው መጥተዋል፡፡ የታመቀውን እና በሌላ መንገድ ሊገለጽ ያልቻለውን ለልቡናቸው ሸክም የሆነ ሐሳብና ስሜት ገጸ ባሕርያቱ በንድፎች (በሚገጣጠሙና በሚለያዩ መስመሮች) ተንፍሰዋቸዋል፡፡


---

[7] እንደወረደ (Stream of consciousness) ሥነ ጽሑፍ ከሥነ ልቡና (ከፍካሬ ልቡና) ወስዶ የገጸ ባሕርያትን ኢ-ንቁ ልቡና ለማየት እንዲያስችል የሚገለገልበት ስልት ነው፡፡ በዚህ ስልት በአእምሮ የሚመጡ ሐሳቦች ቅደም ተከተል ሳይዙ፣ በምክንያትና ውጤት ሳይተሳሰሩ እንዳሻ እንዲፈሱ ይደረጋል፡፡

በገጽ 176 እና 177 ላይ አላዛር የ"ጂኦሜትሪ ቀላል ክርቭ ወይም ቅንፍ" ሲል በገለጸው ድፍንና ግማሽ ጎኑ የተከፈተ የክብ ቅርጽ አስደግፎ የሚያስረዳው ሐሳብ አለ፡፡ በ'ሀ' በወከለውና ዙሪያውን የተዘጋ ባደረገው ክብ ውስጥ ራሱን  አስገብቷል፡፡ እዛ ውስጥ ከእሱ ጋር የእሱና የተባረኪ ትዝታ እንዳለ፣ ያ ትዝታ ደግሞ እንዲነፍስበት ስላልሆነ (ተዘግቶ ስላለ) "መሽተት" እንደሚጀምር ያስረዳል፡፡ እዚህ ጋ ከታመቀና እንዲተነፍስ ካልተደረገ ትዝታ "መጥፎ ሽታ" የመመንጨቱ ሁኔታ ከትራውማ ባሕርይ ጋር ቀጥተኛ መመሳሰል እንዳለው ማስታውስ ይገባል፡፡




ቀጥሎ አላዛር ከታጠረበት "የትዝታ ዝገት" ተላቆ ከሰፊው አለም ጋር ለመገናኘት የክቡን አንድ ግድግዳ በማፍረስ ውስጥ የነበረውን 'ሀ' (ራሱን) ውስጥም ውጭም እንዲሆን ያደርጋል- በምስሉ፡፡




እዚህ ጋ በሰቆቃዊ ገጠመኞቹ ትውስታ እሱ እንደሚለው "የትዝታ ዝገት" የተነሳ የልቡናው መዛልና ከዚያ የመላቀቅ ምኞቱ ነው የተገለጸው፡፡ ምናልባትም ትዝታዎቹን ጨርሶ ሳያጣ ነገር ግን በእነሱም ሳይታሰር የመኖር ምኞቱ፡፡ እንዳሻው ውስጥም ውጭም ለመሆን መሻቱ፡፡

ታቅዶባቸውና ይሁን ተብለው ሳይሆን ድንገት በተገኘው ነገር ላይ የሚሰሩ ቅርጾች፣ ጭረቶች፣ ልዩ ልዩ ምስሎች ወዘተ ከነፍሮይድ ዘመን ጀምሮ በፍካሬ ልቡና ዘንድ ቦታ አግኝተው ጠቀሜታ ላይ መዋል እንደ ጀመሩ መዛግብት  ያስረዳሉ፡፡ ያልታቀደባቸው የድንገቴ ቅርጽና ምስሎች (doodles) ሰዎች ያሉበትን ስሜትና የአእምሮ ሁኔታ ያመላክታሉ፡፡ በተለይ ደግሞ ስሜትን ወይም ሐሳብን እንደ ልብ መግለጽ የማያስችል እክል ሲገጥም ተደጋግመው እንደሚታዩና ወደ ተደበቀ የአእምሮ ሐሳብ መድረሻ በመሆን እንደሚያገለግሉ የተለያዩ ምሁራንን በመጥቀስ Qutub ያስረዳሉ (2012፡ 73)፡፡

ማክዳ ከሰፈሯ ወንዝ ዳር ካለ አሸዋ ላይ የምትስላቸውን ተከታታይና ተገጣጣሚ ምስሎችን (577) ድንገት ነው የምትጀምራቸው፡፡ ምንና ለምን እንደምትሰራ ካለማወቋ የተነሳ አንዱ ላይ ሌላውን እየቀጠለች በሄደች ቁጥር ለምን እንዳደረገችው ትጠይቃለች፤ሆኖም መልስ የላትም፡፡ ምክንያቱም Qutub እንደሚሉት እንዲህ ያሉት ምስሎች የሚሰሩት በንቁ አእምሮ (consciously) አይደለምና ነው (ዝኒ ከማሁ)፡፡



ጭራሮዬን ይዤ ወደ መቀመጫዬ ድንጋይ ልሄድ ስል ሶስት ማዕዘን ስዕል ወይም ትሪያንግል ለስላሳው አሸዋ
ውስጥ ሳልኩ፡፡… በደቂቃዎች እያከታተልኩ ይሄን ሰራሁ፡፡ ይሄን ለምን ሳልኩ?



ከሶስቱ ማዕዘን ስር ካሬ አስገባሁ፡፡ ለምን ካሬ ቀጠልኩ?



ልክ ማለቅ የሚገባው ነገር እንዳለ ሁሉ ከትከሻዬ እስከ ጣቶቼ ባለው የገላዬ ቀበሌ፣ በደመነፍስ ንቅናቄ መስኮቶችና በር ሳልኩ፡፡ ለምን መስኮቶችና በር ሰራሁ?



መንገድ አበጀሁለት፡፡ መንገዱ ወደ ቤት ብቻ አይወስድም፡፡ ራሱ በር ይሆናል፡፡




እዚህ ስደርስ እንዲህ አልኩ፡ አራተኛው ቁራጭ የአንደኛው ትዝታ አለው? ማስታወስ ይችላል? ለምሳሌ ትሪያንግሉ ነጥሎ ያስታውሳል? አንድስ ናቸው? (ገጽ፣ 577)፡፡

ማክዳ ልትሆን ልታሳካ የምትሻውን ከዳር እንዳታደርስ ተደናቅፋ ቀርታለች፡፡ የመጨረሻው ምስል ላይ እንዳሉት ምስቅልቅል ያሉ መስመሮች፤ የቤቱን በር፣ መስኮት፣ መንገድ ሁሉ እንዳጠፉት፤ ያለችበትን ሕይወት ቅርጽና መልክ ለማስያዝ የምታደርገውም ጥረት ክፉ ገጠመኟ ባስከተለባት የልቡና ጉዳት ውል አልይዝ እንዳላት ናት፡፡ ስለ ትላንቷ፣ ስለ ዛሬዋ እንዲሁም ነገዋ መልስ የምትሻበት ብዙ ጥያቄዎች አሏት፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች በዚህ የአሸዋ ስእሏ ላይም መጥተዋል፡፡ ለምሳሌ በመጨረሻው ስዕል ላይ ተከታታይ ጥያቄዎችን ታነሳለች፡፡ “አራተኛው ቁራጭ የአንደኛው ትዝታ አለው?” የሚለው የመጀመሪያው ጥያቄዋ የቀደመውና የንጹው ጊዜ ትውስታዋ ከዛሬ እሷነቷ መራቁን ወይም በኋለኛውና በክፉው ትውስታዋ በእጅጉ መያዟን ያሳስባል፡፡ “ለምሳሌ ትሪያንግሉ ነጥሎ ያስታውሳል? አንድስ ናቸው?” ከሚለው ቀጣይ ጥያቄዋ ውስጥም በትላንትና ዛሬዋ መኃል ጤናማ ትስስር መፈጠር ያለመቻሉን፤ ትላንቷ ከዛሬዋ ሰምሮና ተናብቦ ያለመጓዙን ማንበብ ይቻላል፡፡ በተለይም “ትሪያንግሉ” የምትለው የሶስት ማእዘን ቅርጽ ከሙንጭርጭ መንጻት ቀድሞ ለነበረ ሰላማዊና ጤነኛ ልቡናዋ፣ ከስር ያለውና ኋላ የተሰራው ካሬ በሙንጭርጭ መሞላት ደግሞ ላለችበት የተመሳቀለና ውል ያጣ ልቡናዋ ወኪል ተደርጎ መወሰድ የሚችል ነው፡፡

ስዕሉ የሚያሳየው ሂደትን ነው፡፡ ሂደቱ ደግሞ ደህና እየተገነባ ሄዶ መጨረሻው ምስቅልቅል ባለ፣ ከየት ተነስቶ ወዴት እንደደረሰ በማይታወቅ፣ በተደራረበና በተጣላለፈ፣ የቀደመውን ምስል መልክ ባጠፉ ቅርጽ ነው የሚጠናቀቀው፡፡ ማክዳ መልካም የሆነ ጅማሮ የነበራት ቢሆንም አንዱ ደረጃ ላይ መልካሙ ጅማሬዋ ተስተጓጉሎ ተስፋዋ ተጨናግፏል፡፡ ልቡናዋ ተዘባርቋል፡፡ ይህ የተዘባረቀ የልቡናዋ ምስል እንዲህ ድንገት በሰራችው የአሸዋ ላይ ምስል ወጥቶ መገለጹ የትራውማን ንግግር አልባ ሽብርነት "speechless terror" ማሳያም ነው፡፡ ልትናገረው ያልቻለችውን ጉዳት ነው ድንገቴው ስዕሏ ያወጀው፡፡ እንዲህ ንቁ ባልሆነ አእምሮ የሚነደፉ በግንባታ ሂደት ላይ ያሉ የቤት ምስሎች ሰሪው ያለፈ ሥነ ልቡናዊ የትራውማ ጉዳቱን ለመጠገን የሚፈልግ ሰው መሆኑን እንደሚያሳዩ Qutub የባለሙያዎችን ትንተና ተንተርሰው ያስረዳሉ (2012: 82)፡

መረቅ ትራውማን በማስተማሰል ካነሳባቸው መንገዶች አንዱ የሸፋን ስዕሉ ነው፡፡




በዚህ የሽፋን ስዕል ላይ ከ"መረቅ"፣ "መለልታ" እና "አንጓ" እየተነሱ ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች የሚሄዱ መስመሮች ወይም መንገዶችን እናያለን። ከአንጓ የሚነሳው መንገድ ብቻ አብሮት የሚነሳ ሌላ መንገድ አያጅበውም፣ ብቻውን ነው። የተቀሩት "መለልታ" እና "መረቅ"[8] ግን ከእነሱ በሚነሱ በሶስትና በአራት መስመሮች ይወርዳሉ። ከሶስቱም የሚነሱት መስመሮች ወደ ፊት በሄዱ ቁጥር የሆነ ቦታ ላይ እርስ በርስ የሚገናኙ (አንዱ ሌላውን የሚያቋርጡ) ናቸው። ብዙ ቦታ ላይ ይገናኛሉ። ይነካካሉ፣ ይቀላቀላሉ፤ ከተገናኙበት ቦታ ሲያልፉ ደግሞ በየራሳቸው ይጓዛሉ። ሆኖም ያኔ ከሌላው ተነካክተዋልና ፍፁም ራሳቸውን ናቸው ማለት አይቻልም።

መረቁን ሕይወት ብናደርገው በሕይወት ጉዟችን የሚገጥሙን ያማረ መለልታ (መልካም ገጠኞች)ና መለልታውን የሚያግዱ አንጓዎች (ክፉ ገጠመኞች) ይኖራሉ። ወደ ፊት በቀጠልን ቁጥር የሆነ ቦታ ላይ አንጓ ወይም መለልታ ከመረቃችን (ከሕይወታችን) ይገናኛል። እናም መረቃችን ወይም ሕይታችን ከአንጓም ከመለልታም የተበጀ ይሆናል፤ በደስታና በሀዘን የተሰራ። የመረቁ መስመሮች በቁጥር አራት መሆን በመለልታ (3 መስመሮች) እና በአንጓ (1 መስመር) ድምር የመገኘቱ ማሳያ አድርጎ ማሰብም ያስችላል። ከክፉው መልካሙ ቢበዛም መረቃችንን የሰሩት ግን በድምር ነው። በዚህ ዐይነት መረቃችን መለልታን ብቻ ሳይሆን አንጓንም ይዞ ይጓዛል። እዚህ ላይ ትራውማ ድንገት በመለልታችን የሚሰነቀር የመለልታችንን (የሰላማዊ ሕይወታችንን) ፍሰት አጋጅ አንጓ እንደሆነ ማሰብ ይገባል። መረቅ ውስጥ በንባብ ከገጸ ባሕርያቱ ጋር ስንኖር የምናየውም ይህን ነው።

በመጨረሻ ለትራውማ ትውልድ ተሻጋሪነት የአላዛር አያቶች ይሰሩት የነበረውን ቅል ትዕምርትነት ላንሳ። የአላዛር አያቶች (እናኑና ሰብለ) ቅል ይነግዱ ነበር። በእጃቸው እየነቀሱ የሚያሳምሩት ቅል። "[…] በቅል ላይ በወስፌውም በካራውም ስዕልና ቅርጥ መስራት። ሐረጉን መከየን። መዳፌ በስለት ተቆራርጦ እንደው ወንፊት ይመስል ነበር………." (32) ይላሉ የአላዛር አያት ይሰሩት የነበረውን ሲያጫውቱት። የአላዛር አያቶች የቅል ንግዱን ይሰሩ የነበሩት ከጣልያን ወረራ ቀደም ባለው ጊዜ ነበር። ከዘመናት በኋላ በእነ አላዛር የወጣትነት እድሜ ደርግ የአላዛር አያትን ቤት እስር ቤት ባደረገበት ወቅት እነዚያን ቅሎች እናገኛቸዋለን። ተባረኪ በእስር ላይ በነበረችበት በአንዱ እለት ለጥያቄ ያስጠራት ካድሬ ቢሮ ውስጥ ባረጀ መደርደርያ ላይ ተደርድረው ታያቸዋለች። በቅሎቹ ላይ አይኗ ማረፉን አይቶ በከረጢት ተከተው ተጥለው እንደነበርና ወታደሮቹ እየሰበሩ ሊጨርሷቸው እንደሆነ የሚነግራት ካድሬ አንዷን መርጣ እንድትወስድ ይፈቅድላታል። መፍቀድ ብቻ አይደለም ከተቀመጠበት ተነስቶ አንዷን ቅል በማውረድ በፈገግታ ይሰጣታል (275)።

[8] አዳም በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ አንጓን "ማገጃ"፣ "መታገጃ" ሲል ይፈታዋል። መለልታን ደግሞ "ቀጥታ እርዝማኔ፣ ውጤታው ያማረ" ይለዋል (583)።

ከአምስት አመት በኋላ ተባረኪ ኑሮዋን ከአዲስ አበባ ወደ አዋሳ ለመቀየር ጓዟን ስታዘጋጅ ያችን ቅል እንዳትሰበርባት በጥንቃቄ በልብሶቿ መኃል ስታኖራት መልሰን እናገኛታለን። ቅሏን እንዲህ ስታደርግ ጓዟን ስታሰናዳ ያገኘችውን የማርክሳዊያን መጽሐፍ በማዕድ ቤት እሳት ታስበላለች። ድሮ አበባና ተክሎችን ከምትሰበስብባቸው አልበሞች ሁለቱን አጥታቸዋለች (288)። መጽሐፉን ሆን ብላ አስወግዳዋለች፤ አልበሙ ደግሞ በሌሎች ሰዎች ተወስዶባታል። በአንጻሩ ቅሏ እንደ አልበሞቹ አልጠፋችም፣ እንደ ማርክሳዊ መጽሐፉም ለእሳት አልተወረወረችም። ይልቁንም ወደ አዲስ የመኖሪያ ስፍራዋ፣ ወደ ቀጣይ ሕይወቷ ይዛት ልትጓዝ ታሰናዳታለች።

የቅሏ መነሻ የአያቶቿ ጊዜና ሕይወት ነው። በላይዋ ላይም በዘመኑ ሰው እጅ፣ በዘመኑ ቀለም፣ በዘመኑ ጥበብ የተቀረጸባትን ምስል ይዛለች። የቀራጯ እጆች ጉዳትና ሕመም ሁሉ አለባት። ይህን ሁሉ ይዛ ዘመንና ትውልድ ተሻግራ ተባረኪ ዘንድ የደረሰች የአያት ዘመን ትውስታ ነች። ልሙጥ ቅል አይደለችም፤ የተጻፈ የታተመባት ታሪክ አላትና ስለ ትላንት፣ ስለ ቀራጮቿ የምትናገር፣ የምትተርከው አላት። በአጭሩ ታሪክ ናት ብንላት የሚያስኬድ ይመስለኛል። የዚህችን ቅል ትውልድ ተሻግራ ለተባረኪ መድረስንም እንደ ታሪክ ውርስ ማየት ይቻላል። እዚህ ጋ የታሪክና ትራውማን ትስስር ካስታወስን ተባረኪም ሆነች በእሷ የሚወከለው የዘመኑ ወጣት ትውልድ ከአያቶቹ ትራውማን ጭምር ወራሽ የመሆኑ እውነት ግልጽ ይሆናል። ትራውማ ታሪካዊ ገጽታ እንዳለው ሁሉ ታሪክም ትራውማዊ ተፈጥሮ አለው። ይህን የተገነዘቡት Caruth ታሪክን “history of trauma” ያደርጉታል። በትርጉምና ትንታኔ (referential) የሚደረስበት ነው (1996: 18) ማለት ነው- ልክ እንደ ትራውማ።

ቅሏን ተባረኪ ጋ ለማድረስ የካድሬውን አቀባይ መሆን ምክንያት የለሽ አድርጎ ማለፍ የሚቻል አይመስለኝም። በሁለቱ ትውልዶች መኃል ያለ እንደመሆኑ ካድሬውም ሆነ የሚወክለው ስርአት የትራውማ ሰንሰለቱን በማስቀጠል እንዲሁም ታሪክን በማሻገር ረገድ ሚና እንዳለው ማሰብ ይገባል። ካድሬው አንዷን ቅል መርጦ ለተባረኪ የሚሰጣት ቅሎቹ በባልደረቦቹ ተሰብረው እንዳያልቁ ብሎ ነው። ያን በማድረጉ አንዷ ቅል ተርፋለች። ያችን ቅል በማትረፉ በቅሎቹ ተሰብሮ ማለቅ ልንገነዘብ እንችል የነበረውን የልቡናን ከትራውማ ነጻ መውጣት አስቀርቶብናል። በአንጻሩ ለትውልድ መሸጋገሩን አጉልቶልናል።

### ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በሥነ ጽሑፋዊ የትራውማ ንድፈ ሐሳብ ተመስርቶ ትንተናውን አካሂዷል። ልብ ወለዱ መቼቱ ያደረገው ወቅታዊ ሁኔታ የፈጠራቸውን አሰቃቂ ክስተቶች፣ እነሱን ተከትሎ በገጸ ባሕርያቱ ማንነት፣ አመለካከት፣ የእርስ በርስ ግንኙነት፣ እምነትና አቋም ላይ የተፈጠረውን ቀውስና ለውጥ በዋናነት ተመልክቷል። ከዚህ ሌላ የማይጨበጠውን ሥነ ልቡናዊ ጉዳት (ትራውማ) ተጨባጭ አድርጎ ለመቅረጽ ጥቅም ላይ የዋሉ ገጸ ጽሑፋዊ አቀራረቦችንና ትዕምርቶችን ከትራውማ ባሕርያት ጋር በማዛመድ ትንተናውን ለማካሄድ ሞክሯል።

ትንተናው እንዳመላከተው ግለሰቦችንም ሆነ ማኅበረሰብን ለትራውማ አጋላጭ ያደረጉት ሁኔታዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከወቅቱ የፖለቲካ ስርዓት ጋር ተያይዘው የተከሰቱ ናቸው። ጉዳቱ በግለሰብ ሳይወሰን ማኅበረሰብንም ለማጥቃት የበቃ ሆኗል። የማኅበረሰቡ ለትራውማ መዳረግ የአባላቱን የተናጠል ሕማምና ጉዳት ተገንዝቦ እዲያገግሙ ድጋፍ ለመሆን እንዳይቻለው አድርጎታል። ግለሰቦቹ ለአካላዊና ሥነ ምግባራዊ ጥቃት በመጋለጣቸው ለራስ ያላቸው ክብርና ደረጃ የወረደባቸው፣ ራሳቸውን የሚወቅሱና የሚጸጸቱ፣ በትላንት ክፉ ገጠመኛቸው ትውስታ እየታወኩ ዛሬያቸው ትርጉም ያጣባቸው ሆነዋል። ማኅበረሰቡም ወግና ልማዱ ተቃውሶ፣ ከአቋምና ከእምነቱ ተጣርሶ፣ በሚያወግዝና በሚጸየፋቸው ተግባራት ተጠምዶ፣ የእርስ በርስ ግንኙነቱ ተበላሽቶ ከመለያና መገለጫዎቹ ተነጣጥሏል። በጥቅሉ የወል ማንነት ቀውስ ተፈጥሯል።

የትራውማ ተሻጋሪነትን በተመለከተ ዘመን ተሻግሮ ለቀጣይ ትውልድ የሚተርፍ ሕማም የመኖሩ ጥቁምታዎች ታይተዋል። ከዚህም በላይ ጉልህና በቀላሉ የማይበጠስ ሆኖ የታየው ከተጎጂነት ወደ ጎጂነት የሚደረገው የሽግግር ሰንሰለት ነው። ትላንትና ዛሬ በመልካም ሳይሆን ቂምና በቀልን ባረገዙ ትውስታዎች እንዲተሳሰሩ መሆናቸው ጎልቷል። በውጤቱም እየተኖረበት ያለው ዛሬ ጤና አጥቷል፤ ስለ መጪው ነገ ጤና መሆንም ተስፋ አይታይም።

ከዚህ ሌላ ድርሰቱ በመረጠው የትረካ ስልት፣ በተገለገለባቸው ገጸ ጽሑፋዊ አቀራረቦች እና ትዕምርቶች ትራውማን በወጉ ነድፎ አሳይቷል። ለገጸ ባሕርያቱ የሥነ ልቡና ጉዳትና ትግል ምስል በመፍጠር ረቂቁንና ውስብስቡን ሥነ ልቡናዊ ቁስል ተጨባጭ አድርጎ ቀርጿል። አልነገር፣ ለጽሑፍ አልገራ ባዩን ትራውማ በኪነት ኃይል ወደ ትረካና ትዕምርት በመቀየር መልክና ቅርጽ ሰጥቶ እንዲነበብ፣ እንዲታይ አስችሎታል። በጥቅሉ መረቅ ዘመንና ትውልድ እየተሻገረ በመጣ ጥርቅም ትራውማ ጭምር ልቡናቸው ታውኮ፣ ዛሬያቸውን በራሱ መልክና ጣዕም መኖር ባልቻሉ፣ በትላንትና ዛሬ መኃል ባክነው በቀሩ ገጸ ባሕርያቱ አማካይነት የሕማሙን ተራዛሚ ጉዳት ክሡት ለማድረግ የቻለ ስራ ነው።

ትውስታ በመረቅ ገጸ ባሕርያት ሕይወት ውስጥ ሥፍራው ጉልህ ነው። ይህ መሆኑ እንደ ትራውማ ሁሉ መሰረቱ ትውስታ የሆነውን ኖስታልዥያን (Nostalgia) ያሳስባል። ተጻራሪ ተደርገው ይታሰቡ የነበሩት ሁለቱ ጉዳዮች (ትራውማና ኖስታልዥያ) አሁን በተቃርኖ ከመነሳት ይልቅ ተሳሳቢ እና ተዛማጅነታቸው እየጎላ መጥቷል። አንዱ እንደ ሕማም (ትራውማ)፤ ሌላው ከሕማሙ እንደ መከለያም፣ እንደ መፈወሻም (ኖስታልዥያ) ሆነው መታየት ጀምረዋል። ከ20ኛው ክ/ዘ መጨረሻ ጀምሮ የሥነ ልቡና ባለሙያዎች በኖስታልዥያ አዎንታዊ ጎንና ጠቀሜታ ላይ ማተኮር ይዘዋል። ይህ አካሄድ እንደ ትራውማ ላሉ ሥነ ልቡናዊ ሕማሞች ያለውን ሕክምናዊ ጠቀሜታ ለማጤን አስችሏል (Routledge 2016: 6)። በዚህ እይታ መሰረት ወደፊት ትራውማን ከኖስታልዥያ አጣምሮ በማናበብ ማጥናት አስፈላጊ መሆኑን እጠቁማለሁ።

**ማጣቀሻዎች**


አዳም ረታ። *መረቅ*። አዲስ አበባ፣ ርኆቦት አታሚዎች፣ 2007።

ቴዎድሮስ ገብሬ። 2007 ዓ.ም. "ፍካሬ ልቡናና የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ምንና ምን ናቸው፤ ጌታና ሎሌ? መጻተኛና ቤተኛ? ወይንስ አቻ ለአቻ?"። በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በተዘጋጀ ጉባኤ ላይ የቀረበ፣ ሚያዝያ። ያልታተመ።

Balaev, Michelle. "Literary Trauma Theory Reconsidered." In *Contemporary Approaches in Literary Trauma Theory*, edited by Michelle Balaev, 1-14. UK: Palgrave Macmillan, 2014.

Bell, Duncan. (ed.) *Memory, Trauma and World Politics: Reflections on the Relationship between Past and Present.* New York: Palgrave Macmillan, 2006.

Caruth, Cathy. (ed.) *Trauma: Explorations in Memory*. London: Johns Hopkins UP, 1995.

———————. 1996. *Unclaimed Experience: Trauma, Narrative, and History*. London: Johns Hopkins University Press.

Easthope, Antony. 2001. *The Unconscious.* London and New York: Routledge.

Eyerman, Ron. 2001. *Cultural Trauma: Slavery and the Formation*. New York: Cambridge University Press.

Herman, Judith. 2015. *Trauma and Recovery: From Domestic Abuse to Political Terror*. New York: Basic Books.

Kleber, Rolf J., Charles R. Figley and Berthold P. R. Gersons. 1995. (eds.) *Beyond Trauma: Cultural and Societal Dynamics*. New York: Plenum Press.

Luckhurst, Roger. 2006. "Mixing Memory and Desire: Psychoanalysis, Psychology, and Trauma Theory." In *Literary Theory and Criticism: An Oxford Guide*, edited by Patricia Waugh, 497-507. New York: Oxford University Press.

Moran, Patricia. 2007. *Virginia Woolf, Jean Rhys, and the Aesthetics of Trauma*. New York: Palgrave Macmillan.

Qutub, Afnan. 2012. "Communicating Symbolically: The Significance of Doodling between Symbolic Interaction and Psychoanalytical Perspectives." *Colloquy* 8, 78-85.

Routledge, Clay. 2016. *Nostalgia: A Psychological Resource*. New York: Routledge.

Salter, Jodie. "Intergenerational Storytelling and Transhistorical Trauma: Old Women in Contemporary Canadian Fiction". Diss. University of Guelph. 2012.

Summerfield, Derik.1995. "Addressing Human Response to War and Atrocity: Major Challenges in Research and Practices and the Limitation of Western Psychiatric Models." In *Beyond Trauma: Cultural and Societal Dynamics*, Rolf J. Kleber, Charles R. Figley and Berthold P. R. Gersons. (eds.) 17-29. New York: Plenum Press.

Sztompka, Piotr. 2000. "Cultural Trauma: The Other Face of Social Change." *European Journal of Social Theory* 3(4): 449-466.

Van der Kolk, Bassel and Onno Van der Hart. 1995. "The Intrusive Past: The Flexibility of Memory and the Engraving of Trauma ." In *Trauma: Explorations in Memory*, edited by Cathy Caruth. 158 - 182. Baltimore and London: Johns Hopkins University Press.

Whitehead, Anne. 2004. *Trauma Fiction*. Edinburgh: Edinburgh University Press.

Zepinic, Vito. 2012. *The Self and Complex Trauma*. Bloomington: Xlibris, 2012.